# የጳውሎስ ነገረ–መለኮት

# ትምህርት አራት
# ጳውሎስና የቆሮንቶስ ሰዎች

# The Heart of Paul's Theology
## Lesson Four
## Paul and the Corintians

ተርጓሚ፡ እሸቴ በለጠ
Translator: Eshete Belete

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES
Biblical Education. For the World. For Free.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

# ማውጫ


1. **መግቢያ**

2. **ዳራ**

   ሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞ
   በቆሮንቶስ የነበሩ ችግሮች
      የተበላሹ ግንኙነቶች
      የፍትወት ርኩሰት
      የተዛባ አምልኮ
      የጳውሎስን ሐዋርያዊ ሥልጣን አለመቀበል

3. **አወቃቀርና ይዘት**

   1ኛ ቆሮንቶስ
      ሰላምታ
      ምሥጋና
      መዝጊያ
      ዋናው ጽሑፍ

   2ኛ ቆሮንቶስ
      ሰላምታ
      መግቢያ
      መዝጊያ
      ዋናው ጽሑፍ

4. **ነገረ–መለኮታዊ አመለካከት**

   እምነት
      ክርስቶስን እንደ ጌታ
      ክርስቶስን እንደ አዳኝ

   ተስፋ
   ፍቅር

5. **ማጠቃለያ**

## 1. መግቢያ

አብዛኞቻችን ለጥንታዊው ግሪክ በአፈታሪክ ለኤሶፕ ተሰጥቶ የነበረውን የባህርይ መገለጫ እናውቃለን፡፡ ከእነዚህ አፈታሪኮች በአንዱ፣ "ዔሊና ጥንቸል" በተሰኘው ታሪክ ውስጥ፣ ጥንቸሉ አዘውትሮ ከሁሉ እንስሶች እበልጣለሁ እያለ ይኩራራል፡፡ ስለዚህ፣ በጥንቸሉ ትዕቢት የተሰላቸው ዔሊ፣ እግር ጉዞ ውድድር እናድርግ ሲል ጠየቀው፡፡ እንግዲህ፣ ጥንቸሉ አለኝ በሚለው ትልቅ ችሎታ በመመካት እንደሚያሸንፍ ፍፁም እርግጠኛ ስለነበር በውድድሩ መሃል ላይ ጥቂት እረፍት አደረገ፡፡ ጥንቸሉ በእንቅልፍ ላይ ሳለ፣ ዔሊው ከፊት ለፊቱ ያለውን የማሸነፊያ ገመድ አልፎ ሄደ፡፡

በአንዳንድ መንገዶችም፣ በ1ኛው ክፍለ ዘመን በቆሮንቶስ ከተማ ይኖቹ የነበሩ በርካታ ክርስቲያኖች እንደ አፈታሪኩ ኤሶፕ ዓይነት ሕይወት ነበራቸው፡፡ ገና ውድድሩ ሳይጠናቀቅ ራሱን እንደ አሸናፊ እንደሚቆጥረው እንደ ጥንቸሉ፣ በቆሮንቶስ ይኖሩ የነበሩ በርካታ ክርስቲያኖችም ገና የክርስትና ጉዟቸው ሳይጠናቀቅ ራሳቸውን እነደ አሸናፊ ይቆጥሩ ነበር፡፡ ምድራዊ ሃብታቸውንና የተቀበሏቸውን መንፈሳዊ ስጦታዎች በመመልከት፣ ጌታ ከሁሉ ሰው በላይ እንዳደረጋቸው በማሰብ ራሳቸውን ያስቱ ነበር፡፡ ምድራዊ ሃብታቸው አነስተኛ ከሆነና አስደናቂ መንፈሳዊ ስጦታዎች ካልተሰጣቸው ከተቀሩት ክርስቲያኖች እግዚአብሔር እንደባረካቸው ያስቡ ነበር፡፡

የጳውሎስ ነገረ-መለኮት ከተሰኘው ተከታታይ ትምህርታችን፣ ይህ አራተኛው ትምህርት ሲሆን፣ "ጳውሎስና የቆሮንቶስ ሰዎች" የተሰኘ ርዕስ ሰጥተነዋል፡፡ በዚህ ትምህርት በአሁኑ ወቅት 1ኛ እና 2ኛ ቆሮንቶስ በመባል በሚታወቀው መልእክት ውስጥ እነዚህን ትምክህተኛ ክርስቲያኖች ጳውሎስ እንዴት እንደጻፈላቸው እንመለከታለን፡፡ ምንም እንኳን ሊዳሰሱ የሚገባቸው በርካታ ችግሮች እንዳሉ ጳውሎስ ቢያውቅም፣ እርሱ ግን የችግሮቻቸው ሁሉ ዋነኛ ምንጭ በሆነው ማለትም፡ ሩጫው ገና ሳይፈፀም እነርሱ ግን የክርስትናን ሕይወት የመጨረሻ ሩጫ ሮጠው እንደጨረሱ በተሳሳተ መንገድ በማሰባቸው ላይ ማዕከላዊ ትኩረቱን አድርጓል፡፡

ጳውሎስና የቆሮንቶስ ሰዎች የተሰኘው ጥናታችን በሦስት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ አንደኛ፣ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፋቸውን ደብዳቤዎች ዳራ እንመለከታለን፤ ሁለተኛ፣ የ1ኛ እና የ2ኛ ቆሮንቶስን አወቃቀርና ይዘት እንመረምራለን፤ ሦስተኛ ደግሞ፣ የጳውሎስ መልእክቶች የነገረ-መለኮቱ ማዕከላዊ ሃሳብ የሆነውን ፣ የነገረ-ፍፃሜ አስተምህሮውን እንዴት እንደገለጡ እናያለን፡፡ አስቀድመን ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈውን መልእክት ዳራ እንመልከት፡፡

## 2. ዳራ

በእነዚህ ተከታታይ ትምህርቶች አጽንዖት ለመስጠት እንደሞከርነው፣ ጳውሎስ መልእክቶቹን የጻፈው በተለያዩ አብያተክርስቲያናት የተነሱ ችግሮችን ምላሽ ለመስጠት ነበር፡፡ ስለዚህም፣ 1ኛ እና 2ኛ ቆሮንቶስን ስንመለከት፣ አንዳንድ መሠረታዊ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይገባናል፡ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ምን እየተከናወነ ነበር? ጳውሎስ ለምን ጻፈላቸው? ለእነዚህ ጥያቄዎች በሁለት መንገዶች ምላሽ እንሰጣለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የጳውሎስን ሦስተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ እንቃኛለን፣ ሁለተኛ ደግሞ፣ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተከስተው ወደ ነበሩ አንዳንድ ችግሮች በጥልቀት እንገባለን፡፡ አስቀድመን የጳውሎስን ሦስተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ እንመልከት፡፡

### ሦስተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ

የጳውሎስ ሦስተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ ተመዝግቦ የሚገኘው በሐዋርያት ሥራ 18፡23 እስከ 21፡17 ውስጥ ነው፡፡ በእነዚህ ምእራፎች ጳውሎስ በሁለተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ያዳረሳቸውን ቦታዎች አብዛኞቹን ደግሞ እንደሄደባቸው እንገነዘባለን፡፡ ጳውሎስ ይህንን ጉዞ የጀመረው እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር ወደ 52 እና 53

ዓ.ም. ገደማ ነበር፡፡ እንደ መጀመሪያዎቹ ሁለት ሚሲዮናዊ ጉዞዎች የተነሳው ከሦርያዋ አንጾኪያ ነበር፡፡ ከሐዋርያት ሥራ እንደምንረዳው በገላትያና ፍርግያ የሚገኙ አማኞችን አጠናክሯል፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች ስለ ጎበኛቸው ከተሞች የተነገረን ነገር የለም፡፡ ምናልባትም፣ አስቀድሞ ካገለገለባቸው ከተሞች ቢያንስ አንዳንዶቹን ለምሳሌ፣ በገላትያ የሚገኙትን ደርቤ፣ ልስጥራ፣ ኢቆንየምን አልፎም በፍርግያ የምትገኘውን አንጾኪያንም ጎብኝቷል፡፡ ጳውሎስ በገላትያና በፍርግያ ካለፈ በኋላ ወደ እስያዋ ወይም ወደ ትንሿ እስያ የወደብ ከተማ ወደ ኤፌሶን ተጉዟል፡፡

ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን እንደደረሰም ዐሥራሁለት የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀመዛሙርትን አግኝቶ የክርስቶስ ኢየሱስን ወንጌል በፍጥነት ተቀብለዋል፡፡ ጳውሎስ በመጀመሪያ፣ የሰበከው በምኩራብ ሲሆን፣ ሆኖም በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ፣ አይሁዳውያን መልእክቱን በብርቱ ይቃወሙ ጀመር፡፡ ስለዚህም፣ ለሚቀጥሉት ሁለት ወራት ወንጌል በከተማይቱ ሌሎች ስፍራዎች ሰበከ እግዚአብሔርም አስገራሚ ተዓምራት አደረገ፡፡

በስተመጨረሻም፣ ጳውሎስና ባላንጣዎቹ የታላቋን የኤፌሶን አምላክ የአርጤምስን ቤተመቅደስን ምስሎች በብር በሚቀርፀው ሰው ምክንያት ከፍተኛ ግጭት ውስጥ ገቡ፡፡ በተጨባጭ ማስረጃም ጳውሎስ በርካቶችን ለክርስቶስ ከመማረኩ የተነሳ የጣዖት አምላኪዎቹ ገበያ አሽቆለቆለ፡፡ በውጤቱም ቅርፃ ቅርፅ ሠራተኛውም አመፅ አስነሳ፣ የጳውሎስንም ባልደረቦች ዋስትና ስጋት ላይ ጣሉት፡፡

ከዚህ ክስተት በኋላ፣ ጳውሎስና የጉዞ ባልደረቦቹ በርካታ ወራትን በዘመናችን የግሪክ ግዛት ውስጥ በሚገኙት በመቄዶኒያና በአካይያ አሳለፉ፡፡ በዚህኛው የጳውሎስ ጉዞ ረገድ ጳውሎስ የዘገበው ዘገባ አነስ ያለ ነው፣ ሆኖም ተጓዦቹ ከፊልጵስዩስ ወደ እስያ መመለስ እንደ ጀመሩ ጠቅሷል፡፡ ጳውሎስና ባልደረቦቹ በትራኦስ ቆም አሉ፡፡ በዚያም ለአንድ ቀን ብቻ ለመቆየት ስላሰበ፣ አማኞችን በሌሊት ሰብስቦ አነጋገራቸው፡፡ ጳውሎስም ንግግር ሲያደርግ ሳለ አውጤኪስ የሚባል አንድ ጎበዝ እንቅልፍ ወስዶት ከመስኮቱ ላይ ወድቆ ሞተ፡፡ ሆኖም ግን፣ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ድንቅ አሠራር ሕይወቱ እንዲመለስለት አደረገ፡፡

ጳውሎስና ባልደረቦቹም ትራኦስንም ለቅቀው፣ ወደ ጉረቤት ከተማ ወደ አሶን አቀኑ፣ ከዚያም ወደ ባህር ተመለሱ፡፡ በመንገዳቸውም ሚጢሊኒ፣ ኪዩ እና ሳሞን ቆም ብለው በመጨረሻም ትንሽ ቆይታ ወዳደረጉበት ወደ ሚሊጢን መጡ፡፡ በሚሊጢን ሳሉም ጳውሎስ በአቅራቢያ ወደ ምትገኘው ወደ ኤፌሶን ቤተክርስቲያን መልእክተኞች ልኮ ሽማግሌዎችን አስጠራቸው፡፡ እነርሱንም የሰበሰባቸው የመሰነባበቻ ንግግር ሊያደርግላቸው ደግሞም ሊባረካቸው ነበር፡፡

ከዚህም በኋላ፣ ቡድኑ በመርከብ ተነሳ፡፡ በቆስ፣ በሩድ፣ በጳጥራ፣ በቆጵሮስ አልፈው ጢሮስ ደረሰ፣ በዚያም ለአንድ ሳምንት አገለገሉ፡፡ ከዚያም ወደ ቶለሚስ በመጓዝ፣ ቂሳርያ ደረሱ፡፡ በዚያም አጋቦስ የተሰኘ ነቢይ በኢየሩሳሌም እሥራት እንደሚቆየው ጳውሎስን አስጠነቀቀው፣ ጳውሎስም ያ እውነት እንደሆነ አረጋግጦ ነበር፡፡ ሆኖም፣ ጳውሎስ በአጋቦስ ትንቢትም ሆነ በወዳጆቹ ልመና ሃሳቡን ሳይለውጥ፣ ወደ ኢሩሳሌም አቀና፡፡ ጉዞውንም በ57 ዓ.ም. አካባቢ አጠናቀቀ፡፡

ጳውሎስ በመጽሐፍ ቅዱስ የተካተቱትን ሁለቱን ለቆሮንቶስ ሰዎች የተላኩ መልእክቶቹን የጻፈው በዚህ በሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ሲሆን፣ ተጠብቀው ቆይተው ያላገኘናቸውን ሌሎች ሁለት ደብዳቤዎችንም ጽፏል፡፡ ምናልባት 1ኛ ቆሮንቶስ የተጻፈው ከኤፌሶን ሲሆን ጊዜውም 55 ዓ.ም. አካባቢ ነው፡፡ ይህንን ደብዳቤ ከላከ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ ጳውሎስ ቆሮንቶስን ለአጭር ጊዜ ጎበኘ፣ ሆኖም በዚያ በነበሩ የቤተክርስቲያን አባላት ከፍተኛ ሃዘን ደረሰበት፡፡ ጉብኝቱንም አስከትሎ፣ ጠፍቶ እኛ ያላገኘነውን ደብዳቤ፣ አንዳንዶችም "የሃዘን ደብዳቤ" የሚሉትን ጻፈ፡፡ በኋላም፣ የሃዘኑ ደብዳቤ ያስገኘውን አዎንታዊ ምላሽ ከቲቶ ከሰማ በኋላ፣ ምናልባትም ከመቄዶኒያ ሁለተኛውን የቆሮንቶስን መልእክት፣ ምናልባትም 1ኛ ቆሮንቶስን በጻፈ ባመቱ ወይም በዚያ አካባቢ ጻፈላቸው፡፡

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈው መልእክት ከሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ጋር እንዴት እንደሚጣጣም ካየን፣ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩ አንዳንድ ችግሮችን ወደመመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡ በመካከላቸው ብጥብጥ ያስነሱት ጉዳዮች ምን ነበሩ? ጳውሎስ ለእነርሱ ለምን ደጋግሞ ጻፈላቸው?

# በቆሮንቶስ የነበሩ ችግሮች

የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 18 ስናነብብ፣ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ቤተክርስቲያን የተከለው ቀደም ባለው ሚሲዮናዊ ጉዞው እንደነበርና በዚያን ወቅትም በቆሮንቶስ ለሁለት ዓመታት ከስድስት ወር እንደኖረ እንገነዘባለን፡፡ ሆኖም እርሱ ከሄደ በኋላ ግን የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች አንዳንዶቹን የጳውሎስ ትምህርቶች ረሱ አንዳዶቹንም አላገባብ ተግባራዊ አደረጉ፡፡ በውጤቱም፣ በቤተክርስቲያኒቱ ጠንካራ ግጭቶችና ችግሮች ተከሰቱ፡፡

እንደምንመለከተው፣ በቆሮንቶስ የነበሩ አብዛኞቹ ችግሮች የመነጨት ስለ ነገረ-ፍፃሜ ከነበረ የተሳሳተ መረዳት ሲሆን፣ ያም ክርስቶስ መጪውን ዘመን ማለትም የድነትንና የሕይወትን ዘመን እንዴት እንዳመጣ የተዛባ መረዳት መያዛቸው ነበር፡፡ በርካታ የቆሮንቶስ ሰዎች ከየትኛውም ሰው በበለጠ ሁኔታ በዚያን ወቅት እነርሱ እንደተቀበሉ አምነው ነበር፤ ያስቡ የነበረውም የእግዚአብሔርን የፍፃሜ በረከት በዚያን ወቅት ተቀብለናል ብለው ነበር፡፡

ለእኛ ዓላማ ስንል፣ ይህ የተዛባ መረዳት ወደ አራት ዓይነተኛ ችግሮች እንዴት እንዳመራቸው እንመለከታለን፡ አንደኛ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ የተበለሻሹ ግንኙነቶች፤ ሁለተኛ፣ የፍትወተ ስጋ ርኩሰት፤ ሦስተኛ፣ የተዛባ አምልኮ እና አራተኛ፣ የጳውሎስን ሐዋርያዊ አገልግሎት አለመቀበል ናቸው፡፡ አስቀድመን የተበላሹ ግንኙነቶችን ወደ መመልከቱ እንሸጋገር፡፡

## የተበላሹ ግንኙነቶች

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክት ውስጥ በርካታ የተበለሻሹ ግንኙነቶችን ዳስሷል፣ ለምሳሌ በቤተክርስቲያን ውስጥ ፉክክር፣ በአማኞች መካከል መካሰስ፣ በመካከላቸው ያሉ ድሆችን ቸል ማለት እና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ድሆችን ለማገልገል አለመፍቀድ ናቸው፡፡ አስቀድመን ፉክክሮቹን እንመልከት፡፡

ጳውሎስ 1ኛ ቆሮንቶስን ከመጻፉ አስቀድሞ፣ በቆሮንቶስ አማኞቸ መካከል እርስ በርስ መከፋፈል እንደተፈጠረ የመለያየቱም ምክንያት እኔ የእከሌ፣ እኔ ደግሞ የእከሌ በመባባል ራሳቸውን በጎራ በመክፈል ለመበላለጥ የመፈለግ ፉክክር ነበር፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡12 ውስጥ ጳውሎስ አመለካከታቸውን የገለጠበትን መንገድ እናድምጥ፡

> ***ይህንም እላለሁ፦ እያንዳንዳችሁ፦ እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ እኔስ የአጵሎስ ነኝ፥ እኔ ግን የኬፋ ነኝ፥ እኔስ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ። (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡12)***

እነዚህን አማኞች የከፋፈላቸው በጣም ጥቃቅን ነገር መሆኑ ጳውሎስን አስገርሞታል፡፡ ጳውሎስ፣ አጵሎስ፣ ጴጥሮስ እና ኢየሱስ ሁሉም ያስተማሩት ተመሳሳይ ነገር ነበር፣ ያም ኢየሱስ ከሁሉ የበላይ እንደሆነ ስለዚህም፣ ጴጥሮስን፣ ጳውሎስንና አጵሎስን የመሳሰሉ አስተማሪዎችና ሐዋርያት የእርሱ አገልጋዮች መሆናቸው ነበር፡፡ የእነርሱ ናፍቆት የሃሳብ ፉክክር ትምህርት ቤት መገንባት ሳይሆን፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተክርስቲያን መገንባት ነበር፡፡ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 3፡5 እና 11 እንዲህ ጽፏል፡

> ***አጵሎስ እንግዲህ ምንድር ነው? ጳውሎስስ ምንድር ነው? በእነርሱ እጅ ያመናችሁ አገልጋዮች ናቸው፤ ለእያንዳንዳቸውም ጌታ እንደ ሰጣቸው ያገለግላሉ። … ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (1ኛ ቆሮንቶስ 3፡5፣11)***

ጴጥሮስ፣ ጳውሎስ፣ አጵሎስና ሌሎች ሰብዓዊ መሪዎች ኢየሱስን በሁሉ ይታዘዛሉ፡፡ እነርሱ የሚሠሩት እርሱ አድርጉ ያላቸውን ማለትም፣ ወንጌልን መስበክና የእርሱን ቤተክርስቲያን መገንባት ነው፡፡

የሚያሳዝነው ግን፣ በቆሮንቶስ የነበሩ ክፍፍሎች የፅንሰ-ሃሳብ ክፍፍሎች ብቻ አልነበሩም፤ በቆሮንቶስ የነበሩ ክርስቲያኖች እርስ በርስ እስኪካሰሱና ፍርድ ቤት እስኪሄዱ ያደረሷቸው ነበሩ፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ 6፡7-8 ጳውሎስ ይህንን ሁኔታ እንዴት እንደገለታ አድምጡ፡

*እንግዲህ ፈጽሞ የእርስ በርስ ሙግት እንዳለባችሁ በእናንተ ጉድለት ነው። ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን?*
*ነገር ግን እናንተ ትበድላላችሁ ታታልሉማላችሁ፥ ያውም ወንድሞቻችሁን።*
*(1ኛ ቆሮንቶስ 6፡7-8)*

ይህ አንዳቸው ለሌላቸው ግድ ያለመሰኘት ጉዳይ የጌታን ራት በሚወስዱ ወቅትም ድሆችን ቸል እስኪሉ አድርሷቸዋል፡፡ ጳውሎስ ይህንን ባህርይ በ1ኛ ቆሮንቶስ 11፡21-22 ውስጥ በብርቱ ገስፆታል፡

*በመብላት ጊዜ እያንዳንዱ የራሱን እራት ይበላልና፥ አንዱም ይራባል አንዱ ግን ይሰክራል።*
*የምትበሉባቸውና የምትጠጡባቸው ቤቶች የላችሁምን? ወይስ የእግዚአብሔርን ማኅበር ትንቃላችሁን አንዳችም የሌላቸውን ታሳፍራላችሁን? ምን ልበላችሁ? በዚህ ነገር ላመስግናችሁን? አላመሰግናችሁም። (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡21-22)*

ይህ በራስ ወዳድነት ላይ የተመሠረተ እበልጥ ባይነት በክርስቲያኖች መካከል ወደተፈጠረው አራተኛ የተበላሸ ግንኙነት ያመራል፣ ያም በኢየሩሳሌም ለሚገኙ ክርስቲያኖች ሰብስበው ሊልኩ ቃል ገብተው የነበረውን እርዳታ ቸል እንዲሉ አድርጓቸዋል፡፡ ጳውሎስ 1ኛ ቆሮንቶስን ከመጻፉም አስቀድሞ ይህንን እርዳታ እንዲሰበስቡ ነግሯቸዋል፡፡ ሆኖም 2ኛ ቆሮንቶስን በላከበት ወቅት እንኳን ገና አላጠናቀቁም ነበር፡፡ በ2ኛ ቆሮንቶስ 8፡10-11 ስለዚህ ጉዳይ የሰጠውን ማሳሰቢያ እናድምጥ፡

*በዚህም ነገር ምክር እሰጣለሁ፤ ከአምና ጀምራችሁ ለማድረግ ብቻ ያይደለ ነገር ግን ለማሰብ ደግሞ አስቀድማችሁ የጀመራችሁት ይህ ይጠቅማችኋልና፤*
*አሁንም ለማሰብ በጎ ፈቃድ እንደ ነበረ፥ እንዲሁ እንዳላችሁ መጠን መፈጸም ደግሞ ይሆን ዘንድ፥ ማድረጉን ደግሞ ፈጽሙ። (2ኛ ቆሮንቶስ 8፡10-11)*

በኢየሩሳሌም የሚገኙ ቅዱሳን ጉድለት የመሙላት ፍላጎት እንዲያድርባቸው ጳውሎስ ያሳስባቸዋል፣ ከዚያም አልፎ በ2ኛ ቆሮንቶስ 8-9 የገቡትን ቃል እንዲፈፅሙ ጉዳዩን በማንሳት በጽኑ ያሳስባቸዋል፡፡

## የግብረ-ሥጋ ርኩሰት

ከተበላሹ ግንኙነቶች በተጨማሪ፣ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ሥርዓተ ፆታዊ ችግሮች በይፋ ይታዩ ነበር፡፡ በጥቅሉ፣ በርካታ የቆሮንቶስ ሰዎች ኢየሱስ ስለመጣ፣ ጾታዊ ጉዳዮች ይህንንም ያህል ፋይዳ የላቸውም ብለው ያምኑ ይመስላሉ፡፡ ከዚህም አስተሳሰብ የተነሳ፣ ሁለት የተለያዩ ፅንፍ የያዙ ፆታዊ ልምምዶች አቆጠቆጡ፡፡ በአንድ በኩል፣ አንዳንዶቹም በቤተክርስቲያን ውስጥ የግብረ ሥጋ ልቅነትን የሚፈቅድ አመለካከት አዳበሩ፡፡ ይህም ለበርካታ ችግሮች መንስዔ ሆነ፣ ያም ግብረ-ሰዶማዊነትንና ምንዝርናን ያካትታል፡፡ ጳውሎስ ግን

ነጥሎ አንድን ችግር ይጠቅሳል፤ ያም የአባቱን ሚስት ያገባ ሰው መኖሩ ነው፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ 5፡1-2 ጳውሎስ ይህንን ሁኔታ ያወገዘበትን መንገድ አድምጡ፡

*በአጭር ቃል በእናንተ መካከል ዝሙት እንዳለ ይወራል የዚያም ዓይነት ዝሙት በአሕዛብስ እንኳ የማይገኝ ነው፥ የአባቱን ሚስት ያገባ ሰው ይኖራልና። እናንተም ታብያችኋል፤ ይልቅስ እንድታዝኑ አይገባችሁምን? ይህን ሥራ የሠራው ከመካከላችሁ ይወገድ። (1ኛ ቆሮንቶስ 5፡1-2)*

በዚህ አውድ፣ *echo* (e;cw) የተሰኘው የግሪክ ቃል፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በማድረግ አብሮ መኖርን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ ሰው ከአባቱ ሚስት ጋር እያደረገ ያለውን የግብረ-ስጋ ግንኙነት ቸል በማለታቸው ይመካሉ ስለዚህም የቆሮንቶስ ሰዎች ነገረ-መለኮታቸው ግራ የገባው ነበር፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ በቆሮንቶስ የነበሩ አንዳንደ ክርስቲያኖች በተቃራኒው ጽንፍ ውስጥ ነበሩ፣ ማለትም ምናኔን እና በትዳር ውስጥ እንኳን ከግብረ-ሥጋ መታቀብን መርጠው ነበር፡፡ ጳውሎስ ይህንንም በእጅጉ አውግዞታል፣ ምክንያቱም ይህ ተግባር የጋብቻን ቃል ኪዳን የሚያፈርስና ባልና ሚስቱን ለትልቅ የፍትወተ ሥጋ ፈተና የሚያጋልጥ ስለሆነ ነው፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ 7፡2-5 እንዲህ ጽፏል፡

*ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት።*
*ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ።*
*ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ።*
*ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ። (1ኛ ቆሮንቶስ 7፡2-5)*

በዚህም ስፍራ *echo* (e;cw) የተሰኘው የግሪክ ቃል ሚስት ትኑረው በሚል ተተርጉሟል፡፡ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው፣ ይህንን በመሰለው አውድ ውስጥ *echo* (e;cw) በግብረ-ስጋ ግንኙነት አብሮ መኖር የሚለውን ሃሳብ ነው የሚይዘው፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ ባልና ሚስት አግባብነት ባለው የግብረ-ስጋ ግንኙነት የትዳራቸውን ዓላማ እንዲያሳኩና ራሳቸውንም ከዝሙት ፈተና እንዲጠብቁ ያሳስባክ፡፡

## የተዛባ አምልኮ

በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበረው ሦስተኛው ችግር በአምልኮ ወቅት ያልተገባ ነገር ማድረግ ነበር፡፡ ከዚህም ነገር አንደኛው በጌታ ራት ወቅት ችግረኞችን ቸል ማለት እንደሆነ አስቀድመን ተመልክተናል፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ ሌሎች ሦስት ችግሮችም አቆጥቁጠው ነበር፡፡ እነርሱም፣ ፆታዊ ሃላፊነትን ቸል ማለት፣ የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀም እና ለጣዖት የተሰዋ ስጋ ናቸው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ጳውሎስ ያሳሰበው ጉዳይ ወንዶችና ሴቶች በጋራ አምልኮ ወቅት የሚሳዩት ባህርይ ነበር፡፡ አንዱም የሰጠው እርማት በጸሎት ወቅት ራስን የመከናነብ ጉዳይ ነበር፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ 11፡4-5 እንዲህ ጽፏል፡

*ራሱን ተከናንቦ የሚጸልይ ወይም ትንቢት የሚናገር ወንድ ሁሉ ራሱን ያዋርዳል። ራስዋን ሳትሸፍን ግን የምትጸልይ ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት ሁሉ ራስዋን*

*ታዋርዳለች፤ እንደ ተላጨች ያህል አንድ ነውና። (1ኛ ቆሮንቶስ 11፡4-5)*

ምሁራኑ ጳውሎስ እየተናገረ ያለው በጸሎት ወቅት ስለሚለበስ የራስ መሸፈኛ ነው ወይስ ስለ ጸጉር አሠራር ነው በሚለው ስምምነት የላቸውም:: ከዚህ ባሻገር ራሱን ያዋርዳል ማለት ምን ማለት ነው በሚለወ ስምምነት የላቸውም:: አንዳንዶች፣ ራስ የሚያመለክተው የአካል ክፍል የሆነውን ነው ሲሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ የወንድ ራስ ክርስቶስ ነው የሴት ራስ ደግሞ ወንድ ነው የሚለውን ለማመልከት የገባ ነው ይላሉ:: ሆኖም ግን ይህ ቃል ማንንም ይወክል ማንንም፣ የተሰመረበት ጉዳይ ግልጽነው፣ ወንዶችና ሴቶች በአምልኮ ወቅት ያልተገባ ባህርይ ያሳዩ ነበር:: ይህም በፆታዎቹ መካከል አግባብነት ያለው የመለያ ድንበር ያልነበረው ነበር ማለት ነው::

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፣ በአምልኮ ወቅት ሊኖር ስለሚገባው የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀም ጳውሎስ ያነሳል:: በግልጽ እንደሚታየው በርካታ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችእንደ ልሳንና ትንቢት መናገር የመሳሰሉ አስደናቂ ስጦታዎች ስለተቀበሉ ደግመው ደጋግመው በአምልኮ አገልግሎት ውስጥ ያለአገባብ ይጠቀሙባቸዋል:: በ1ኛ ቆሮንቶስ 14፡26-33፣ ይህንን ጉዳይ እንዲህ ሲል ጳውሎስ ገልጾታል፡

*እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ምንድር ነው? በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ*
*መዝሙር አለው፥ ትምህርት አለው፥ መግለጥ አለው፥ በልሳን መናገር አለው፥*
*መተርጐም አለው፤ ሁሉ ለማነጽ ይሁን።*
*በልሳን የሚናገር ቢኖር ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ አንዱም*
*ይተርጕም፤*
*የሚተረጕም ባይኖር ግን በማኅበር መካከል ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር*
*ይናገር።*
*ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ ሌሎችም ይለዩአቸው፤*
*በዚያ ለሚቀመጥ ለሌላ ግን አንድ ነገር ቢገለጥለት ፊተኛው ዝም ይበል።*
*ሁሉም እንዲማሩ ሁሉም እንዲመከሩ ሁላችሁ በእያንዳንዳችሁ ትንቢት ልትናገሩ*
*ትችላላችሁ።*
*የነቢያትም መናፍስት ለነቢያት ይገዛሉ፤ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡26-33)*

በዚህ ስፍራ ከተገለጹት የጳውሎስ ቃላት እንደምንገነዘበው፣ በቆሮንቶስ የነበረው የአምልኮ አገልግሎት ሥርዓት የሌለውና ግራ የሚያጋባ ነበር፣ በአንድ ጊዜ ብዙ ሰዎች ይናገራሉ:: አማኞች አንዳቸው ሌላቸውን ካላደመጡና የሚለየውን ካልለዩ፣ መንፈስ ቅዱስ ከሚሰጣቸው ቃል ሊያገኙ የሚገባቸውን አያገኙም በማለት ጳውሎስ ያሳስባል::

በሦስተኛ ደረጃ፣ ለጣዖት ከተሰዋ ሥጋ ጋር የተያያዘውን ጉዳይ መጥቀስ ይገባናል:: በጥንታዊው ዓለም፣ በገበያ ላይ የሚሸጥ ሥጋ አስቀድሞ ለጣዖት ተሰጥቶ ወይም ተሰውቶ ነበር፣ እናም ስጋ ይገኝ የነበረው ከአህዛብ መቅደሶች ነበር:: እንግዲህ፣ ጳውሎስ እያለ ያለው የአህዛብ የአምልኮ ልምምድ ሥጋን ሊያረክስ አይችልም፣ ስለዚህ ክርስቲያኖች የሚያደርጉትን ከአህዛቡ አምልኮ ጋር ለመቀላቀል ሲሉ አያድርጉት እንጂ ስጋውን ለምግብነት ብቻ ገዝተው መመገብ ይችላሉ ነው:: ሆኖም ደግሞ ክርስቲያኖች በሚበሉበት ጊዜ አዕምሯቸው በተሳሳተ አስተሳሰብ ከተያዘ አማኞችም ጣዖት አምላኪ ሊሆኑ እንደሚችሉ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል:: በ1ኛ ቆሮንቶስ 8፡7 ይህንን ጉዳይ ዳሶታል፡

*ነገር ግን ይህ እውቀት በሁሉ ዘንድ አይገኝም፤ አንዳንዶች ግን ጣዖትን እስከ አሁን ድረስ ስለ ለመዱ፦ ለጣዖት የተሠዋ ነው ብለው ይበላሉና ሕሊናቸው ደካማ ስለ ሆነ ይረከሳል። (1ኛ ቆሮንቶስ 8፡7)*

በቀላሉ ስናስቀምጠው፣ በቆሮንቶስ የሚገኙ ክርስቲያኖች በደካማ ነገረ-መለኮታዊ እውቀት ለጣዖት የተሰዋን ሥጋ በመብላት ለክርስቶስ የሚያቀርቡትን አምልኮ ለአህዛብ አማልክት ከሚቀርብ አምልኮ ጋር ቀይጠውታል፡፡ ጳውሎስ በተጨማሪም ብርቱ የሆኑት ክርስቲያኖች በአመጋገባቸው ደካማ ወንድሞቻቸውን ይበልጥ ግራ በማጋባት ኃጢአትን እንደሠሩ አመልክቷል፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ 8፡10 እና 12

> *አንተ እውቀት ያለህ በጣዖት ቤት በማዕድ ስትቀመጥ አንድ ሰው ቢያይህ፥ ደካማ ሰው ቢሆን ለጣዖት የተሠዋውን ለመብላት ሕሊናው አይታነጽበትምን? … እንዲህም ወንድሞችን እየበደላችሁ ደካማም የሆነውን ሕሊናቸውን እያቆሰላችሁ ክርስቶስን ትበድላላችሁ።*
> *(1ኛ ቆሮንቶስ 8፡10 እና 12)*

በዚህ መንገድ ለአማኞች ግድ ባለመሰኘታቸው፣ ለደካማ ወንድሞቻቸው ኃጢአት እነርሱም ተጠያቂነት አለባቸወ ማለት ነው፡፡

በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነበረው እጅግ በርካታ አግባብነት የጎደለው ተግባር ጳውሎስን እጅግ ያሳስበው እንደነበር ማየት እንችላለን፡፡ የነዚህ ሁሉ ችግሮች ስሩ ግን ራስ ወዳድነት እና ልበ ደንዳናነት መሆኑን በውል እናስተውላለን፡፡ ራሳቸውን ከልቅነት ማላቀቅ አልቻሉም፣ ልቅነታቸው ሌሎች አማኞችን ለአስከፊ ኃጢአት ለጣዖት አምልኮ አሳልፎ እየሰጠ እንኳን ሊያቆሙ አልቻሉም፡፡ ወደ ኋላ ላይ በዚህ ትምህርት እንደምናየው፣ ሌሎችን ማክበርንና ስፍራ መስጠትን ቸል ማለታቸው አምልኳቸውን ከንቱ እንደሚያደርግባቸውን እንደሚስወቅሳቸው እንረዳለን፡፡

## የጳውሎስን ሐዋርያዊ ስልጣን አለመቀበል

ልንመለከተው የሚገባን አራተኛው ችግር የጳውሎስን ሐዋርያዊ ሥልጣን አለመቀበላቸውን ነው፡፡ ይህኛው እንዲያውም ትልቁ ችግራቸው ነው፡፡ ቀደም ብለን እንዳነበብነው በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡12 ውስጥ፣ በቆሮንቶስ ይኖሩ የነበሩ አንዳንዶች የየራሳቸውን የመሮካከሪያ ታላላቅ ሰዎች በማንሳት የጳውሎስ ሥልጣን ያቃልሉ ነበር፡፡ ገና ያልተመለከትነው ግን እስከ መጨረሻው ሊያቃልሉት የሚፈልጉትን ለማሳፈር በሁለቱም መልእክቶች እንዴት አድርጎ የሐዋርያነት ሥልጣኑን ጳውሎስ እንደገለጠ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ 9፡1-3 እንዲህ ጽፏል፡

> *እኔ ነጻ አይደለሁምን? ሐዋርያስ አይደለሁምን? ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስንስ*
> *አላየሁትምን? እናንተስ በጌታ ሥራዬ አይደላችሁምን?*
> *የሐዋርያነቴ ማኅተም በጌታ እናንተ ናችሁና ለሌሎች ሐዋርያ ባልሆን ለእናንተስ ምንም*
> *ቢሆን ሐዋርያ ነኝ።*
> *ለሚመረምሩኝ መልሴ ይህ ነው። (1ኛ ቆሮንቶስ 9፡1-3)*

በ2ኛ ቆሮንቶስ 12፡11-12 ደግሞ፣ እንዲህ ብሏል፣

> *በመመካቴ ሞኝ ሆኜአለሁ፤ እናንተ ግድ አላችሁኝ፤ እናንተ እኔን ልታመሰግኑ ይገባ ነበርና። እኔ ምንም ባልሆን እንኳ፥ ከዋነኞቹ ሐዋርያት በምንም አልጎድልምና። በእርግጥ የሐዋርያነት ምልክት በመካከላችሁ በምልክትና በድንቅ ነገር በተአምራትም በሁሉ ትዕግሥት ተደረገ። (2ኛ ቆሮንቶስ 12፡11-12)*

አንዳንዶቹ የቆሮንቶስ ሰዎች ያለ ልክ በራሳቸው ትዕቢት ጢም ብለዋል ስለዚህም ለእነርሱ መለወጥ የሆነውን ሐዋርያ ሥልጣን ክደዋል፡፡ በርሱ ምትክ፣ "ዋነኞቹ ሐዋርያት" ብለው የሚጠሯቸውን በእርግጥም ሐዋርያ ያልሆኑትን ተከተዋል፡፡

እነዚህ ሐሰተኛ ሐዋርያት እንደ ጳውሎስና እንደተቀሩት አግባብነት እንዳላቸው ሐዋርያት ተመሳሳይ ሥልጣን አለን ይላሉ፡፡ አብዛኞቹን የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ኃጢአት ወደሞላበት መንገድና አኗኗር የሚከትት ሐሰተኛ ወንጌል ይሰብካሉ፡፡ በ2ኛ ቆሮንቶስ 11፡12-15፣ እነዚህን ክፉ ሰዎች እንዲህ በማለት በብርቱ ይወቅሳቸዋል፡

> ***ነገር ግን በዚያ በሚመኩበት እንደ እኛ ሆነው ሊገኙ፥ ምክንያትን ከሚፈልጉቱ ምክንያትን እቆርጥ ዘንድ አሁን የማደርገውን ከዚህ ወዲህ ደግሞ አደርጋለሁ።***
> ***እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ፥ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኮለኞች ሠራተኞች ናቸውና።***
> ***ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና።***
> ***እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል። (2ኛ ቆሮንቶስ 11፡12-15)***

ጳውሎስ እነዚህን አጭበርባሪ ሰዎች በጣም ከባድ በሆነ ቋንቋ ገስጿቸዋል ምክንያቱም ውሸታቸው ከባድ ዳፋ ስለሚያስከትል ነው፡፡ የቆሮንቶስ ሰዎች ሐሰተኛዎቹን ሐዋርያት ካመኑና የጳውሎስን ትምህርት ከተቃወሙ፣ ክርስቶስንና ወንጌሉን መቃወማቸው ነው፡፡

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ ከበርካታ ችግሮች ጋር እንደተጋፈጠ ማየት እንችላለን፡፡ ወደፊት እንደምናየው፣ እነዚህ ችግሮች በ1ኛ እና በ2ኛ ቆሮንቶስ መልእክቶች ውስጥ ዳር እስከዳር የጳውሎስን ሃሳብ የያዙ ነበሩ፡፡

# 3. አወቃቀርና ይዘት

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈውን መልእክት ቅርፅ የሚሰጡልንን ወሳኝ ጉዳዮች ዳራ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ የደብዳቤዎቹን ይዘት ወደመመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰፈሩትን ሁለቱን የቆሮንቶስ መልእክቶች ዋና ዋና ክፍሎቻቸውን ጠቅለል አድርገን በማየት እንዳስሳቸዋለን፡፡ አስቀድመን በ1ኛ ቆሮንቶስ እንጀምር፡

## 1ኛ ቆሮንቶስ

1ኛ ቆሮንቶስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈው ሁለተኛው ደብዳቤ እንደሆነ እናውቃለን፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ 5፡9፣ "በመልእክቴ ጻፍሁላችሁ" የሚለው ቃል፣ ቀድሞ የጻፈው ደብዳቤ እንዳለ ጳውሎስ መጠቆሙን ያሳያል፡፡ የቆሮንቶስ ሰዎችም ለጳውሎስ ደብዳ ጽፈውለታል፣ ይህም በ1ኛ ቆሮንቶስ 7፡1 ተጠቅሷል፡፡ እናም 1ኛ ቆሮንቶስ በበርካታ ነጥቦች በቤተክርስቲያኒቱ ደብዳቤ ላይ የተጠቀሱ ጉዳዮችን የሚዳስስ ይመስላል፡፡

አንደኛ ቆሮንቶስ በአራት ዋና ክፍሎች ተዋቅሯል፡ ሰላምታ በ1፡1-3 ውስጥ፤ ምሥጋና 1፡4-9 ውስጥ፤ ለደብዳቤው የተሰጡ ምላሾችን የያዘው ዋናው አካልና ዘገባ በ1፡10-16፡12 እና መዝጊያ በ16፡13-24 ናቸው፡፡

## ሰላምታ

ሰላምታው አጠር ያለ ሲሆን፣ ደብዳቤው ከጳውሎስና ከሶስቴንስ እንደተጻፈና ተቀባይዋም በቆሮንቶስ የምትገኘው ቤተክርስቲያን እንደሆነች ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም እንደ ሰላምታ የሚያገለግል በረከትም ተካትቶበታል፡፡

## ምሥጋና

ምሥጋናው ደግሞ ይበልጥ አጭር ሲሆን፣ የቆሮንቶስ ሰዎች ስላላቸው እምነት፣ ስለተቀበሉት መንፈሳዊ ስጦታ እና ስለመዳናቸው ጳውሎስ ያለውን መተማመንና አድናቆት ይገልፃል፡፡

## መዝጊያ

መዝጊያው ጥቅል የሆኑ ማሳሰቢያዎችን፣ እስጢፋኖስንና ቤተሰቡን መቀበሉን፣ የመጨረሻ ሰላምታ፣ ቡራኬ እና የዳብደቤውን ተዓማኒነት ያረጋገጠበት በራሱ በጳውሎስ የእጅ ጽሑፍ መጻፉን የጠቀሰበትን ጉዳዮች አካትቷል፡፡

## ዋናው አካል

ዋናው አካል ሁለት ንዑሳን ክፍሎችን ይዟል፡፡ ከምዕራፍ 1 ቁር 10 እስከ 6፡20 ጳውሎስ ከቀሎዔ ቤተሰዎች ለደረሰው ሪፖርት የሰጠውን ምላሽ ይዟል፡፡ ከ7፡1-16፡12 ደግሞ፣ ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ለተላከለት ደብዳቤ የሰጠውን ምላሽ ይዟል፡፡ ከሁለቱ ንዑሳን ክፍሎቸ በመጀመሪያው፣ ጳውሎስ ከቀሎዔ ቤተሰዎች ባገኘው መልእክት ትኩረቱን የሳቡ ሦስት ጉዳዮችን ዳስሷል፡፡ እነርሱም፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ መከፋፈል፤ ርኩሰት እና ክርስቲያን ከነማን ጋር ይተባበር የሚሉ ናቸው፡፡

ቀደም ብለን እንዳየነው፣ የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን መከፋፈልን የፈጠሩባት በርካታ ችግሮች ነበሩባት፡፡ የጳውሎስ፣ የጴጥሮስ፣ የአጵሎስና የኢየሱስ ነን በመባባል ተገነጣጥለወ ነበር፡፡ በፍርድ ቤትም እርሰ በርሳቸው በመካሰስ ተከፋፍለው ነበር፡፡ በመካከላቸው ያሉና በኢየሩሳሌም የሚገኙ ችግረኞችን ቸል በማለት ክፋታቸውን ገልጠው ነበር፡፡ ጳውሎስ እነዚህን ችግሮች የተጋፈጠው በተለያዩ መንገዶች ነው፡፡

ለምሳሌ፣ ኢየሱስ ተቀዳሚ መሪያቸው እንደሆነ ደግሞም ሐዋርያትንና አስተማሪዎችን እንደ ክርስቶስ አገልጋዮች በእርግጥ የሚቆጥሩ ከሆነ፣ የቆሮንቶስ ሰዎች ከሐዋርያትና ከአስተማሪዎች መካከል አንዳንዶቹን በመምረጣቸው ምክንያት ሊከፋፈሉ አይችሉም በማለከት መከራከሪያውን ያቀርባል፡፡ ለቤተክርስቲያን ሐዋርያትና አስተማሪዎች ከፍተኛ ግምት ከመስጠታቸው የተነሳ ከሌሎቹ ሁሉ እጅግ የሚልቀውን ኢየሱስን መመልከት አልቻሉም፡፡

ጳውሎስ በተጨማሪም መንፈሳዊ ጉዳዮችን በአግባቡ መምራትን አስመልክቶ ምድራዊ ጥበብ እጅግ ደካማ መሆኑን በዝርዝር አመልክቷል፡፡ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ በሌላው ማኅበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ባለጠጎች እና የተማሩት በጣም አናሳ ቢሆኑም በግልጽ ተፅዕኖ ፈጣሪ ነበሩ፡፡ በእነርሱም አመራር ስር የተቀረችው ቤተክርስቲያን በምድራዊው እሴት መሠረት እንድትመራ አድርገው ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ በ1፡19-20 እንዲህ ጽፏል፣

***የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ የአስተዋዮችንም ማስተዋል እጥላለሁ ተብሎ***

*ተጽፎአልና።*
*ጥበበኛ የት አለ? ጻፊስ የት አለ? የዚች ዓለም መርማሪስ የት አለ? እግዚአብሔር የዚችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን? (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡19-20)*

የቆሮንቶስ ሰዎች እንደ ዓለማውያን በማሰባቸው ሞኞች መሆናቸውን ከማመልከት ባሻገር፣ መንፈሳዊ ብስለት የጎደላቸው መሆኑንም እንዲያውቁ አድርጓል፡፡ በ 3፡1-2 ውስጥ እንዲህ ጽፏል፡

*እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፥ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም። ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ (1ኛ ቆሮንቶስ 3፡1-2)*

በሌላ አገላለጽ፣ የተከፋፈሉት የቆሮንቶስ ሰዎች በጥበባቸውና በብስለታቸው የበለጡ እንደሆኑ ቢያስቡም፣ እውነታው ግን ምንም የማያውቁ መሆናቸው ነው፣ እንዲያውም የእግዚአብሔርን ህዝብ ወደ መምራት ብቃት የተጠጉ እንኳን አልነበሩም፡፡ ዓለማዊ እሴቶቻቸው ለመንፈሳዊ እውነት እውር እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡

ጳውሎስ በተጨማሪም በደረሰው ሪፖርት ላይ ተመሥርቶ የቆሮንቶስ ሰዎች ስለታየባቸው ርኩሰት ተጠያቂ ያደርጋቸዋል፡፡ ከአባቱ እናት ጋር ስለተኛው ሰው ጉዳይ ቀደም ብለን አንስተናል፡፡ ጳውሎስ ያንን ጉዳይ ያነሳው በ5፡1-13 ውስጥ ነው፡፡ ስለጉዳዩ በጣም ጥቅል ሃሳብ የጻፈው ግን በ6፡12-20 ውስጥ ሲሆን፣ የቆሮንቶስ ሰዎች በገሃድ "ሁሉ ተፈቅዶልኛል" የሚል መፈክር አንግበው እንደነበር እንረዳለን፡፡ ጳውሎስ ይህንን መፈክራቸውን ውድቅ ያደረገው በቁጥር 12 እና 13 ውስጥ እንዲህ በማለት ነበር፡

*ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን አይጠቅምም። ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም። መብል ለሆድ ነው፥ ሆድም ለመብል ነው፤ እግዚአብሔር ግን ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል። ሥጋ ግን ለጌታ ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም፤ ጌታም ለሥጋ ነው፤ (1ኛ ቆሮንቶስ 6፡12-20)*

እንደተመለከትነው፣ አንዳንድ የቆሮንቶስ ሰዎች አሁን ኢየሱስ ስለመጣ የትኛውም ዓይነት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ተፈቅዷል ብለው ያስቡ ነበር፡፡

ጳውሎስ በምዕራፍ ስድስት ውስጥ የሆነ ስፍራ ላይ የቆሮንቶስ ሰዎች ወደ ክርስቶስ ከመምጣታቸው አስቀድሞ በልዩ ልዩ የግብረ-ስጋ ኃጢአቶች የታወቁ እንደነበሩ ጠቅሷል፣ ይህም ሴሰኝነት፣ ዝሙት፣ የወንድና የሴት አዳሪነት ደግሞም ግብረ-ሰዶማዊነትን ያካትታል፡፡ ምንም እንኳን፣ አስረግጦ መናገር ባይቻልም፣ ስለ ርኩሰት የጻፈው ጉዳይ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ አሁንም እነዚያን በመሰሉ ልምምዶች ውስጥ የነበሩትን በቀጥታ እንደሚመለከት እናስባለን፡፡ ምንም ይሁን ምን፣ ከአባቱ ሚስት ጋር የተጋባውን ሰው ቤተክርስቲያን ዝም የማለቷ ነገር በዚህ ረገድ የነበሩበትን ቸልተኝነት ያሳያል፡፡

በመጨረሻም፣ ጳውሎስ አስቀድሞ ክርስቲያኖች ከነማን ጋር ኅብረት ሊያደርጉ እንደሚገባቸው የሰጠውን መመሪያ ማብራሪያ ይሰጥበታል፡፡ በዓለም ከሚኖሩ ከማያምኑ ሰዎች ጋር ተስማምተው እንዲኖሩ ይፈልጋል፣ ሆኖም አማኞች ነን እያሉ በኃጢአት ከተነከሩትና ለእግዚአብሔር ህዝብ አሳፋሪ ድርጊት ከሚፈጽሙት ማለትም ከአባቱ እናት ጋር ተጋብቶ ከሚኖረው ሰው ዓይነቶች እንዲርቁ ያሳስባቸዋል፡፡ እነዚህን በመሳሰሉ ጉዳዮች፣ የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን አግባብነት ያለውን የሥነ-ስርዓት ርምጃ ልትወስድ ይገባታል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም በደለኛውን ከቤተክርስቲያን ማባረርንም ሊያካትት ይችላል፡፡ ይህንን መመሪያ በ5፡9-11 ጠቅለል አድርጎታል፡፡

*ከሴሰኞች ጋር እንዳትተባበሩ በመልእክቴ ጻፍሁላችሁ። በጠቅላላው የዚህን ዓለም ሴሰኞችን፥ ወይም ገንዘብን የሚመኙትን ነጣቂዎችንም፥ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩትን አላልሁም፤ ይህስ ቢሆን ከዓለም ልትወጡ ይገባችሁ ነበር። አሁን ግን ወንድሞች ከሚባሉት አንዱ ሴሰኛ ወይም ገንዘብን የሚመኝ ወይም ጣዖትን የሚያመልክ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካር ወይም ነጣቂ ቢሆን ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ እጽፍላችኋለሁ፤ እንደነዚህ ካለው ጋር መብል እንኳን አትብሉ። (1ኛ ቆሮንቶስ 5፡9-11*

የ1ኛ ቆሮንቶስ ዋና አካል ሁለተኛ ክፍል ከ7፡1-16፡12 ድረስ የሚዘልቅ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ስለ ጋብቻ ጉዳይ ለላኩለት ጥያቄ ጳውሎስ የሰጠው ምላሽ በ7፡1-40 ድረስ ይገኛል፤ ከምዕራፍ 8-10 ደግሞ፣ ለጣዖት ስለተሰዋ ሥጋ የሚናገረው ይገኛል፤ ስለ አምልኮ የሚናገረው ደግሞ በ11፡2-34 የሚገኝ ሲሆን ይህኛው ግን የቆሮንቶስ ሰዎች ላቀረቡት ጥያቄ ምላሽ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አልተጠቀሰም፤ በምዕራፍ 12-14 ውስጥ ስለ መንፈሳዊ ስጦታ፤ ምዕራፍ 15 ደግሞ የአማኞችን ትንሣኤ ርዕሰ ጉዳይ ያስተዋውቃል፤ በ16፡1-12 ውስጥ በኢየሩሳሌም ለምትገኘው ቤተክርስቲያን እና ስለ አጵሎስ የሚናገረው ይገኛል፡፡

ጋብቻን፣ ድጋሚ ጋብቻንና አለማግባትን አስመልክቶ ጳውሎስ ምላሽ የሰጠበት ጥያቄ የመጀመሪያው ጥያቄ ነው፡፡ ጳውሎስ ይህንን ሃሳብ ያነሳው በ7፡1-40 ውስጥ ነው፡፡ በቆሮንቶስ የሚኖሩ አንዳንድ አማኞች በጋብቻ ውስጥ እያሉ እንኳን ምንኩስናንና የግብረ ሥጋን ተዓቅቦ ይለማመዱ ነበር፡፡ ስለ ምንኩስና አንዳንድ የቆሮንቶስ አማኞች የነበራቸው ዝንባሌ በጋብቻ ውስጥ ሊኖር የሚገባውን የግብረ-ስጋ ግንኙነት ከጥያቄ ውስጥ የማስገባትና የትዳርን ክቡርነት የማቃለል ዝንባሌ እንዲያቆጠቁጥ አድርጎ ነበር፡፡ ለዚህም ምላሽ ይሆን ዘንድ፣ ጳውሎስ ጋብቻንም አለማግባትንም በየፈርጃቸው የዳሰሰ ሲሆን፣ ሰው ከተጋባ ግን በውስጡ የግብረ-ስጋ ግንኙነት እንዳለበት ማረጋገጫ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ጳውሎስ ያለማግባት ከማግባት ይልቅ ጠቀሜታ እንዳለውም ጠቆም አድርጓል፣ ምክንያቱም አለማግባት “በጌታ ጉዳይ ላይ” ማለትም በክርስቶስ መንግሥት ጉዳይ ላይ ለማትኮር ይረዳል የሚል ነው፡፡ አንዳንድ አማኞች ጳውሎስ ለብቻ የመሆንን ጠቃሚነት የጠቀሰው በትዳር ውስጥ ቀውስ ሲፈጠር ነው ሲሉ፣ የተቀሩት ደግሞ ክርስቶስ በመጀመሪያ ከመጣበት ጊዜ አንስቶ እስከ ዳግም መመለሱ ድረስ የሚገኙ ክርስቲያኖችን ሁሉ ይመለከታል ይላሉ፡፡

በምዕራፍ 8-10 ውስጥ፣ ጳውሎስ የዳሰሰው ለጣዖት ስለ ተሰዋ ሥጋ ነው፡፡ በጣዖታት መቅደሶች ሥጋ ይቀርብ እንደነበረ ተነጋግረናል፣ ያም የምዕራፍ 8 ዋና ርዕስ ነው፡፡ ሆኖም በመደበኛው ልምምድ፣ የአህዛብ መቅደሶች ያረዱዋቸውን እንስሳት ስጋ ሙሉ በሙሉ ለአምልኮው አይቀሙበትም፣ ስለዚህ የተረፈውን ለሽያጭ ያውሉታል፡፡ ስለዚህም፣ በምዕራፍ 10 ውስጥ፣ ጳውሎስ የጻፈው ከገበያ ስለሚገዛው ስጋ ነው፡፡ ጳውሎስ እየተከራከረ ያለው ያንን ስጋ ገዝተው ስለሚበሉት ክርስቲያኖች ሲሆን፣ መከራከሪያውም ያንን ያደረጉት የአህዛብ አምልኮ አካል ለመሆን አስበው እስካልሆነና ከጎሊናቸው ጋር በመጣላት እስካልሆነ ድረስ የሚል ነበር፡፡ ሆኖም ድርጊታቸው በሌሎች ሲታይ ከጣዖት አምልኮ ጋር እንደተያያዘ ከተቆጠረ ሊበሉ እንደማይገባቸውም አስተምሯል፡፡ በምዕራፍ ዘጠኝ ያነሳውን የገላጋይነት መልእክት፣ በክርስትናው ያገኘውን ነፃነት እንኳን ላለመጠቀም ያለውን ፈቃደኝነት በመግለጽ፣ ሌሎችም ይህንኑ እንዲያደርጉ ይጠይቃል፡፡

በምዕራፍ 11 ውስጥ፣ ጳውሎስ ከአምልኮ ጋር ተያያዥነት ወዳላቸው ሁለት ጉዳዮች ይሸጋገራል፡፡ እነርሱም፣ ፆታዊ ሃላፊነቶች ከቁጥር 2 እስከ 16 የዳሰሰው እና በጌታ ራት ወቅት ድሆችን ቸል ማለት፣ ከቁጥር 17 እስከ 34 ባለው ውስጥ እንደጠቀሰው ማለት ነው፡፡ ይህንን የመሰለው ትዕቢት እና ራስ ተኮርነት በቤተክርስቲያን ውስጥ መገነጣጠልን፣ መካሰስን፣ በምግብ ምክንያት ለደካማ ክርስቲያኖች እንቅፋት መሆንንና በአምልኮ ወቅት ክርስቲያኖች እርስ በርስ የማይከባበሩ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ የሰጠው የመፍትሄ ሃሳብ ይህንን አስከፊ ባህርይ የሚያስወግድ ብቻ ሳይሆን ልብን በመለወጥ ላይ ያተኮረ ቢሆን አያስገርምም፡፡

በምዕራፍ 12-14 ውስጥ፣ ጳውሎስ የዳሰሰው ከመንፈሳዊ ስጦታዎች አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ነው፡፡ በምዕራፍ 12 ውስጥ፣ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን የሚሰጠው የስጦታውን ተቀባዮች ለማግነን ወይም ለጻድቃኖች ሽልማት አድርጎ እንዳልሆነ ያብራራ ሲሆን ይልቁኑ ስጦታውን የሚሰጠው ለቤተክርስቲያን እንደሚያስፈልግ እንደሆነ ገልጿል፡፡

በተለምዶ “የፍቅር ምዕራፍ” ተብሎ በሚታወቀው፣ በምዕራፍ 13 ውስጥ፣ ሁሉም መንፈሳዊ ስጦታዎች በፍቅር አገልግሎት ላይ ሊውሉ እንደሚገባ ጳውሎስ ያብራራ ሲሆን፣ በዚህ መንገድ ተግባር ላይ ካልዋሉ እርባና እንደሌላቸው ገልጿል፡፡

በመጨረሻም፣ በምዕራፍ 14 ውስጥ በሥርዓት አልበኝነት ስለተሞላው አምልኳቸው ጳውሎስ የገሰጻቸው ሲሆን፣ በጋራ አምልኮ ወቅት መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን እንዴት ሊጠቀሙባቸው እንደሚገባ መመሪያ ሰጥቷል፡፡

ምዕራፍ 15 ደግሞ የአማኞችን ትንሣኤ ጉዳይ አስተዋውቋል፡፡ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን የሚገኙ አንዳንዶች አማኞች በአካል ከሞት ይነሣሉ የሚለውን አስተምህሮ በግልፅ ይክዱ ነበር፡፡ ለዚህ ግድፈት ምላሽ ለመስጠት ሲል፣ የክርስቶስ ትንሣኤ የወንጌል ቁልፍ ነገር መሆኑን ጳውሎስ ካብራራ በኋላ፣ አማኞች የመጨረሻ መዳናቸውን ለመቀበል ኢየሱስ እንደተነሣ እነርሱም ሊነሡ ይገባል በማለት እርግጡን ያስቀምጣል፡፡

ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎች ላቀረቡለት ጥያቄ የሰጠውን ምላሽ ያጠናቀቀው በ16፡1-12 ሲሆን በዚያም በኢየሩሳሌም ለምትገኘው ቤተክርስቲያን እርዳታ እንዴት ሊሰበስቡ እንደሚገባ ጥቂት መመሪያ ይሰጥና ስለ አጵሎስ ደግሞ ጥቂት ማብራሪያ ያቀርባል፡፡

የ1ኛ ቆሮንቶስን ይዘት ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወደተካተተው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ወደ ጻፈው ሁለተኛ መልእክት ይዘት ትኩረታችንን ዘወር ማድረግ ይገባናል፡፡

## 2ኛ ቆሮንቶስ

ሁለተኛው የቆሮንቶስ ሰዎች መልእክት በተለያዩ መንገዶች ይዋቀራል፡፡ እኛ ግን ይዘቱን በአራት ዋና ርዕሶች ስር እንዳስሰዋለን፡ ሰላምታ በ1፡1-2 ውስጥ፤ መግቢያ በ1፡3-11 ውስጥ፤ ዋናው አካል በ1፡12-13፡10 እና መዝጊያውን በ13፡11-14 ናቸው፡፡

### ሰላምታ

ደብዳቤው ከጳውሎስና ከጢሞቴዎስ የተላከ እንደሆነ፣ ተቀባዮቹ ደግሞ በቆሮንቶስ የምትገኘው ቤተክርስቲያን እና በአካይያ ግዛት ዙሪያ የሚገኙ ቅዱሳን እንደሆኑ ሰላምታው ይገልጻል፡፡ እንደ ሰላምታ የሚያገለግለውን አጭር ቡራኬም አካትቷል፡፡

### መግቢያ

ቤደብዳቤዎቹ መግቢያን የማካተቱ ነገር የጳውሎስ መለያ ነው፡፡ ይህ መግቢያ ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ ሲል እያለፈበት ስላለው ብርቱ መከራ፣ ደግሞም ከእግዚአብሔር ስለተቀበለው መጽናናት ይገልጻል፡፡ በተቀዳሚነት የቆሮንቶስ ሰዎች ከጳውሎስ ሙግት ጋር እንዲጣጣሙ ማድረግን ዒላማ ያደረገ ሲሆን፣ ስለ ወንጌል ብለው መከራ ለሚቀበሉ አማኞች ሁሉ መጽናኛም ሆኖ ያገለግላል፣ እንዲያውም ጌታን ራሱን “የመጽናናት ሁሉ አምላክ” በማለት ይጠቅሰዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ በመከራ ውስጥ ያሉ ሰዎች ከእነርሱ መጽናናት ሌሎችም መከራ የሚቀበሉ ሰዎች እንዲጽናኑ ያበረታታል፡፡

## መዝጊያ

መዝጊያው በጣም አጭር ሲሆን፣ ጥቂት ጠቅለል ያሉ ማሳሰቢያዎችንና የስንብት ሰላምታ ያካተተ ነው፡፡

## ዋና አካል

ዋናው አካል የደብዳቤውን ግዙፍ አካል የያዘ ሲሆን አምስት ዋና ንዑስ ርዕሶችን አካትቷል፡ የጳውሎስ ባህርይ መከላከያ በ1፡12-2፡11 ውስጥ፤ ለኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ስለሚሰበሰበው እርዳታ የሰጠው መመሪያ በ7፡2-9፡15 ውስጥ፤ የጳውሎስ አገልግሎት ቀጣይ መከላከያ በ10፡1-12፡13 ውስጥ እና ስለ ጳውሎስ ቀጣይ ጉብኝት የሚያወሳው በ12፡14-13፡10 ውስጥ ይገኛሉ፡፡

በ1፡12-2፡11 ውስጥ፣ ጳውሎስ ስለ ድርጊቱ መሟገቻ አቅርቧል፡፡ በመጀመሪያ፣ አስቀድሞ አቅዶ እንደነበረው፣ ለምን ቆሮንቶስን እንዳልጎበኘ አብራርቷል፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ከቆሮንቶስ ሰዎች አንዱ ስላደረሰበት በደል ተረናግሯል፡፡ በግልጽ እንደምናየው፣ ጳውሎስ ቆሮንቶስን የመጎብኘት እቅድ እንዳለው ይፋ ካደረገ በኋላ፣ በእርሱና በቆሮንቶስ በሚገኙ አንዳንዶች መካከል ግጭት ተፈጥሯል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ጎብኝቷቸው ቢሆን ኖሮ፣ ጉብኝቱ ፊት ለፊት መጋጠም ያለበት፣ እንዲያውም የሥነ-ስርዓት እርምጃ የሚወስድበት ይሆን እንደነበር ጳውሎስ ያውቃል፡፡ ስለዚህም፣ ጳውሎስ ለመታገሥ ሲል፣ የጉዞ እቅዱን ለወጠ፡፡ በቆሮንቶስ የነበሩ በርካታ ክርስቲያኖች ይህ ተግባር የምህረት ተግባር መሆኑ ሊያስተውሉ አልቻሉም፣ እንዲያውም በትእግሥቱ ተበሳጩ፡፡ አንዳንዶቹም ተዓማኒነቱን ጥያቄ ውስጥ አስገቡ፡፡

ምን ያህል ተያያዥነት እንዳለው ባናውቅም፣ ጳውሎስ በተጨማሪም በእርሱ ላይ በደል የፈፀመና ቤተክርስቲያንም በተከታታይነት ቅጣት ስለበየነችበት አንድ አማኝ ጉዳይም አንስቷል፡፡ ጳውሎስ ሰውየውን ይቅር እንዳለውና እስካሁን የተላለፈበት ቅጣት በቂው እንደሆነ ጳውሎስ ለቤተክርስቲያን ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡ እናም ቤተክርስቲያኒቱ ለሰውየው ፍቅሯን እንድትገልጽለትና ወደ ኅብረታቸውም እንዲመለስ እንዲፈቅዱለት ትእዛዝ ያስተላልፉል፡፡

በ2፡12-7፡1 ውስጥ፣ በጣም ከበድ ያለን ጉዳይ ይዳስሳል፡፡ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን የነበሩ አንዳንዶች የጳውሎስን ሐዋርያነት መጠራጠራቸውን ገፉበት፡፡ አስቀድመን እንደተመለከትነው፣ ጳውሎስ ይህንን ጉዳይ በ1ኛ ቆሮንቶስ ዳስሶታል፡፡ ሆኖም በ2ኛ ቆሮንቶስ ከሚገኘው ንግግሩ እንደምንረዳው፣ በቆሮንቶስ ሚገኙ በርካቶች ስለ ስህተታቸው ንስሓ አልገቡም፡፡ ስለዚህ፣ ሰፋ ባለ መልኩ ስለ አገልግሎቱ መከራከሪያ ያቀርባል፣ በዚያም ጥሪውና ሥልጣኑ ከእግዚአብሔር እንደሆነ እና የሐዋርያነት ሥልጣኑን መቃወም ብርቱ ቅጣት እንደሚያስከትል ግልጽ ያደርግላቸዋል፡፡

እንዲያውም፣ በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡18፣20 ውስጥ፣ በጣም ርቆ በመሄድ ሐዋርያነቱን የሚቃወሙ ሰዎች አልዳኑም እስከማለት ድረስ ሃሳብ ሰንዝሯል፡

> *ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤*
> *እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ።*
> *እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን። (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡18-20)*

ከእግዚአብሔር ጋር ያልታረቁ ሰዎች የኃጢአታቸውን ሸክም ዛሬም እንደተሸከሙ ናቸው፣ ምህረትን አልተቀበሉም፡፡ በእርግጥም፣ ኢየሱስ ራሱ የእርሱን አምባሳደር አለመቀበል ማለት እርሱን አለመቀበል ማለት እንደሆነ አስተምሯል፡፡ ጌታ በሉቃስ 10፡16 ለአገልጋዮቹ እንደነገራቸው፡

> ***የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል፥ እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል፤ እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል።***
> ***(ሉቃስ 10፡16)***

ይህ ጉዳይ በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነው ጳውሎስም በደብዳቤው ውስጥ ጉዳዩን በተለያዩ መንገዶች ዳስሶታል፡፡ በመጨረሻም እጅግ የሚወድዳቸው የቆሮንቶስ ሰዎች እንዲያውቁለት የሚፈልገው ወንጌሉን በመቃወማቸው ምክንያት ሞት እንደሚጠብቃቸው ነው፡፡

ሦስተኛው ንዑስ ክፍል ከ7፡2 -9፡15 የሚዘልቀውና በኢየሩሳሌም ለምትገኘው ቤተክርስቲያን ስለሚሰበሰበው እርዳታ መመሪያ የሰጠበት ክፍል ነው፡፡ በዚህ ወቅት በኢየሩሳሌም የነበሩ ክርስቲያኖች በታላቅ ችግር ውስጥ ነበሩ፣ ምክንያቱም በይሁዳ ተከስቶ የነበረው ረሃብ ነው፡፡ ለዚህ ችግር ምላሽ ለመስጠት፣ የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ከሌሎች አብያተክርስቲያናት ጋር በመሆን፣ ለእነርሱ እርዳታ ለመላክ ራሳቸውን ሰጡ፡፡ ሆኖም የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን የገባችውን ቃል መፈፀም ተሳናት፣ እርዳታውንም መሰብሰብ አቃታት፡፡ ስለዚህም፣ ጳውሎስ፣ ስሌሎች መስዋዕት የመሆንን አስፈላጊነት በሰፊው አብራራላቸው፡፡ አስቀድሞ የሚያነሳው የመቄዶኒያ አብያተክርስቲያናት በዚህ ረገድ ያሳዩትን ተምሳሌት ሲሆን፣ እነርሱም ከአቅማቸው በላይ እንደሰጡና በዚህም ጉዳይ የበኩላቸውን ማበርከት በመቻላቸው ትልቅ ደስታ ተሰምቷቸው ነበር፡፡ በተጨማሪም የቆሮንቶስ ሰዎች ዛሬ እያጣጣሙት ያለውን በረከት ስላስገኘላቸው የክርስቶስ መስዋዕትነት ያነሳላቸዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ ቀደም ብሎ የነበራቸውን ሃሳብ ቢፈፅሙ እግዚአብሔር በብዙ እንደሚባርካቸው በማንሳት የቆሮንቶስን ሰዎች ያበረታታቸዋል፡፡

በ 10፡1-12፡13 ድረስ፣ ጳውሎስ እንደገና ስለሐዋርያነቱ መከራከሪያ ያነሳል፡፡ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መሪዎቻቸው በዓለም መስፈርቶች ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸውን ክህሎቶች የተላበሱ እንዲሆኑ ይጠብቃሉ፣ ጳውሎስ ደግሞ እነዚያን የሚለማመድ ባለመሆኑ በቆሮንቶስ በሚገኙ በበርካቶች ዘንድ ትምህርቱና ሥልጣኑ ዋጋ እንደሌለው ተቆጠረ፡፡ ለምሳሌ፣ የቆሮንቶስ ሰዎች ስልጡን ለሆኑ ተናጋሪዎች መሪዎቻቸው ደመወዝ እንዲቆርጡላቸው ይጠብቁ ነበር፡፡ ጳውሎስ ግን ደመወዝ መቀበል አልፈለገም፣ በቆሮንቶስ በነበረ ወቅት ለቤተክርስቲያን ሸክም ላለመሆን ሲል ራሱን በገንዘብ ይደግፍ ነበር፣ በዚህም ምክንያት እንደ ዝቅተኛ ሰው ተቆጠረ፡፡

ለዚህም ዝንባሌ ምላሽ ለመስጠት፣ ጳውሎስ የብቃት ማረጋገጫዎቹን በማቅረብ፣ የአገልግሎቱን አግባብነት ከማረጋገጥ ባሻገር የቆሮንቶስ ሰዎችም አግባብነት ለሌላቸው እሴቶች ስፍራ በመስጠታቸው ይወቅሳቸዋል፡፡ ከሌሎቹ በተጨማሪ፣ ስለ ወንጌል ሲል የከፈለውን አስደናቂ መስዋዕትነት፣ ሰማያትን ሳይቀር የማየት እድል ማግኘቱን ይጠቅሳል፡፡ ከዚህም በዘለለ፣ አሁን ወደ ማጥቃቱ ይሸጋገርና የቆሮንቶስ ሰዎች ካላቸው ምድራዊ ማስረጃ የተነሳ ከበሬታ የሚሰጧቸውን በቆሮንቶስ የሚገኙ የሐሰት ሐዋርያት ስለሚያስራጩት ውሸት ያቃልላቸዋል፡፡ ስለ እነዚህ ሰዎች ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 11፡13-14 ውስጥ እንዲህ ጽፏል፡

> ***እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ፥***
> ***ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኮለኞች ሠራተኞች ናቸውና።***
> ***ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን***
> ***ይለውጣልና። (2ኛ ቆሮንቶስ 11፡13-14)***

ሐሰተኛ ሐዋርያትን የሰይጣን አገልጋዮች ብሎ በመጥራት፣ አማኝ እንዳልሆኑ እና ዋሾ መሆናቸውን ጳውሎስ ግልጽ በማድረግ እነርሱን የሚያደምጡ ሁሉ ራሳቸውን አደጋ ውስጥ ይከትታሉ፡፡

በመጨረሻም፣ በ 12፡14-13፡10 ውስጥ፣ ቀጣዩ ጉብኝቱን አስመልክቶ የሰጠውን መግለጫ ጳውሎስ ያቀርባል፡፡ ጉብኝቱ ለቤተክርስቲያኒቱ የፍርድ ትርጓሜ ቢሰጠውም እንኳን ወደ ቆሮንቶስ ለመምጣት ወስኗል፡፡ የሚያሳዝነው፣ አማኝ ነን ብለው የሚናገሩ እና እጅግ በከፉ በደሎቻቸው ደጋግመው የተወቀሱ ግን ስለ በደላቸው ንስሓ መግባትን አሻፈረኝ ያሉ በርካታ ሰዎችን ሊያገኝ እንደሚችል ገምቷል፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ መልእክቱን የሚያነብቡ ሁሉ አሁንም በእምነት የጸኑ መሆን አለመሆናቸውን እንዲመዝኑ መመሪያ ይሰጣል፡፡ በ13፡5 ውስጥ የተናገረውን እናድምጥ፡

> ***በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ፤ ወይስ ምናልባት የማትበቁ ባትሆኑ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ እንዳለ ስለ እናንተ አታውቁምን? (2ኛ ቆሮንቶስ 13፡5)***

አማኝ ነን ብለው ያመኑ በርካቶች ምናልባትም በእውነት ለድነታቸው በክርስቶስ የሚታመኑ ላይሆኑ እንደሚችሉ ጳውሎስ ያውቃል፡፡ ስለዚህም ተቃዋሚዎቹ እውነተኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ይሆናሉ የሚል ተስፋ በመሰነቅ ለቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን የንስሓን፣ የእምነትንና የመዳንን ወንጌል በጽናት ሰበከላቸው፡፡

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፋቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ የተካተቱ መልእክቶች ዳራና ይዘት በአጭሩ ከዳሰስን፣ አሁን ደግሞ ወደ ሦስተኛው ጉዳያችን ማለትም በ1ኛ እና በ2ኛ ቆሮንቶስ መልእክቶች የተገለጠውን የጳውሎስን ነገረ-መለኮታዊ አመለካከት ወደ ማየቱ እንሸጋገራለን፡፡

# 4. ነገረ-መለኮታዊ አመለካከት

በዚህ ትምህርት እስከዚህ ነጥብ ድረስ፣ ጳውሎስ በ1ኛ እና በ2ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ ያነሳቸውን ልዩ ልዩ ችግሮች ዳሰሰናል፡፡ የቆሮንቶስ ሰዎች ስለ ነገረ-ፍፃሜ የነበራቸው ደካማ አስተሳሰብ በነዚህ ችግሮች ላይ ብርቱ ጫና እንደፈጠረ ሃሳብ አቅርበናል፡፡ የጳውሎስ ነገረ-መለኮት በተሰኙት ቀደም ባሉት ትምህርቶች እንዳየነው ሁሉ አሁንም ጳውሎስ ተደራሲያኑን ለማረም የመጨረሻው ዘመን አስተምህሮውን የተጠቀመባቸውን መንገዶች እንዳስሳለን፡፡

በእነዚህ ትምህርቶች እንደጠቆምነው፣ የጳውሎስ ነገረ-ፍፃሜ እግዚአብሔር ታሪክን ቀንበቦበታል ብለው አይሁዳውያን በሚያራምዱት አመለካከት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን፣ ገዢ የነበረው አይሁዳዊ ግንዛቤ ብሉይ ኪዳን ታሪክን በሁለት ይከፍለዋል ይህም "የአሁን ዘመን" እና "መጪው ዘመን" የሚል ነው፡፡ የአሁን ዘመን አሁን የምንገኝበት የኃጢአት፣ የፍርድ እና የሞት ዘመን ሲሆን፣ "መጪው ዘመን" ግን የእግዚአብሔር ህዝብ የሚቀበለውን ከፍተኛ በረከትና እግዚአብሔር በጠላቶቹ ላይ የሚበይነውን የመጨረሻ ፍርድ የሚያሳየው የወደፊት ጊዜ ነው፡፡ በእነዚህ ዘመናት መካከል ሽግግር የሚደረግበት ዘመን ደግሞ "የመሲሁ" ወይም "የክርስቶስ" የመምጣት ዘመን ነው፡፡ መሲሁ ሲመጣ፣ የአሁኑን ዘመን ያጠናቅቅና መጪውን ዘመን ይጀምራል፡፡

እርግጥ ነው፣ የአይሁድ ነገረ-መለኮት በሚጠብቀው መጠን ታሪክ እንዳልተከናወነ ጳውሎስን እና ሌሎችን ሐዋርያትን የመሳሰሉ የክርስቶስ ተከታዮች አውቀዋል፡፡ ከየትኞቹም ጥርጣሬዎች ባሻገር፣ ኢየሱስ መሲሁ ነበር ደግሞም መጪውን ዘመን አብስሯል፡፡ ይመጣሉ ተብለው ተስፋ የተሰጠባቸውን በረከቶች በሙላት ገና አልፈጸመም፡፡ በአጭሩ፣ የምንኖርበት ዘመን የዘላለም መዳን የምንቀበልበት ዘመን በአንዳንድ መንገዶች አሁን እዚህ "መጥቷል"፣ ግን ደግሞ በአንዳንድ መንገዶች "ገና" ነው ማለት ነው፡፡ አሁን እኛ ያለንበት ዘመን የአሁን ዘመንና መጪው ዘመን በጉድኝት የሚጓዙበት ዘመን ነው፡፡ ሁለቱም በጣምራ በሚኖሩበት ዘመን፣ የመጪውን

ዘመን በረከቶች በመጠኑ እናጣጥማለን፣ ደግሞም የዚህ የኃጢአትና የሞት ዘመን ዳፋ የሆኑት መከራና ስቃይ እንደሚኖርብንም ልንገነዘብ ይገባናል፡፡

ይህ የነገረ-ፍጻሜ ንድፍ በመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ ችግሮችን እንደፈጠረ ጳውሎስ አውቋል ምክንያቱም መጪው ዘመን በምን ያህል መጠን አሁን አዚህ እየሆነ እንዳለ ቁርጡ ስለማይታወቅና ለግምት ስለሚተው ነው፡፡ ቀደም ባሉት ትምህርቶች፣ አንዳንድ አማኞች ይህንን ጉዳይ ወደ አንድ ጽንፍ እንደወሰዱት ተመልክተን ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ የተሰሎንቄ ሰዎች ያለመጠን የጋለ ነገረ-ፍፃሜን አዳብረው የነበረ ሲሆን፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ ኢየሱስ ይህንን ዘመን ያስወግድና መጪውን ዘመን በሙላት ያመጣል ብለው ያምኑ ነበር፡፡ በውጤቱም፣ በዚህ ዘመን የሚኖረው ሕይወት እጅግም አስፈላጊ አይደለም ብለው ያስቡ ነበር፡፡ በሌላ ጎኑ፣ የገላትያ ሰዎች ደግሞ መጪው ዘመን ወሳኝ በሆነ መንገድ አልመጣም የሚል አቋም ነበራቸው፡፡ ይህንን ግድፈታቸውንም "ነገረ-ፍጻሜን ያለመገንዘብ" ብለነዋል፡፡

በቆሮንቶስ የነበረውን ችግርና ጳውሎስ ለችግሮ የሰጣቸውን ምላሾች በቅርበት ስንመለከት፣ የቆሮንቶስ ሰዎች የዘመናቱን ዒላማ በትክክለኛው መንገድ የመገንዘብ ችግር እንደነበረባቸው እናያለን፡፡ በልቡናቸው፣ የኃጢአትና የሞት ዘመን የሆነው የአሁኑ ዘመን ሊያከትም ነው፣ እነርሱም የመጪውን ዘመን የተትረፈረፉ በረከቶች ለመቀበል ነፃ ወጥተናል ብለው ያስባሉ፡፡ ስህተታቸውም "ያለ ልክ የጋለው ነገረ-ፍፃሜ" አንዱ መገለጫ ነው፡፡ ስለዚህም፣ በቤተክርስቲያናቸው ስለ ነበሩት ጉዳዮች ጳውሎስ ሲናገር፣ "ባለው" እና "በሚመጣው" ዘመን መካከል ሕይወታቸውን እንዴት እየመረመሩ ሊጓዙ እንደሚገባቸው አስተምሯቸዋል፡፡

ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች ችግሮች የዳሰሰባቸው በርካታ መንገዶች ቢኖሩም፣ እኛ ግን በደብዳቤዎቹ ውስጥ ጎላ ብለው በተገለጡት ሦስት የነገረ-ፍፃሜ ውቅረ-ነገሮች ላይ እናተኩራለን፡፡ እነርሱም፡ እምነት፣ በተለይም ክርስቶስ የበላይ ከመሆኑ አንፃር፤ ተስፋ በአሁኑ ዓለም ሳይሆን በወደፊቱ ላይ፤ ፍቅር ለክርስቲያናዊ አኗኗር ወሳኝ ውቅረ-ነገር የሚሉ ናቸው፡፡ ጳውሎስ በክርስቶስ ከሁሉ የበላይነት ላይ አጽንዖት በመስጠት ሚዛን የሳተውን የቆሮንቶስ ሰዎች እምነት ለማከም የሄደባቸውን መንገዶች አስቀድመን እንመልከት፡፡

# እምነት

በዚህ ትምህርት የቆሮንቶስ ሰዎች ትምክህት እና ግትርነት በቤተክርስቲያን ውስጥ በርካታ ችግሮችን እንደፈጠረ ተመልክተናል፡፡ በትልቁ፣ ይህ ግትርነት የተፈጠረው የቆሮንቶስ ሰዎች ክርስቶስ በሁሉ ላይ ጌታ እና አዳኝ እንደሆነ ካለመመልከታቸው የተነሳ ነው፡፡ ከክርስቶስ ጌትነት አንፃርም እርሱ መንግሥቱን ወደ ሙላት ሊያመጣና ሊገዛ ሥልጣን እንዳለው  አጽንዖት መስጠት ተስኗቸዋል፡፡

## ክርስቶስን እንደ ጌታ

ምንም እንኳን ነገሩ ግራ ቢመስልም፣ አንዳንድ የቆሮንቶስ ሰዎች ክርስቶስ የእግዚአብሔርን መንግሥት በሙላት አምጥቷታል፣ ስለዚህም በርካታውን የመንግሥቱን በረከቶች እያጣጣምን ነው እንዲያውም እግዚአብሔር ለአማኞች ካዘጋጀው በረከት ምንም የቀረብን የለም ብለው ያስቡ ነበር፡፡ በተጨማሪም ኢየሱስ በመሠረተው ምድራዊ መንግሥት ገዢዎች እንዳደረጋቸው አድርገው ይንቀሳቀሱ ነበር፡፡ ይህም ሃሳብ ጎልቶ ይታይ የነበረው በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሥልጣን ባላቸው ሰዎች መካከል ነበር፡፡ ክርስቶስ ይህን ሥልጣን የሰጣቸውም ከሌሎች ይልቅ እነርሱ ጥበበኞችና የላቁ መንፈሳውያን ስለሆኑ እንደሆነ ይገምቱ ነበር፡፡ እናም በእነርሱ ዕይታ፣ እነዚህን ታላላቅ ብድራቶች ሊቀበሉ የተገባቸው አይደሉም የሚሏቸውን ያቃልሉ ነበር፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ 4፡7-10 ይህንን የመሰለውን አስተሳሰብ ጳውሎስ የገሰፀበትን መንገድ እናድምጥ፡

*አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ*

*ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው?*
*አሁን ጠግባችኋል፤ አሁንስ ባለ ጠጎች ሆናችኋል፤ ያለ እኛ ነግሣችኋል፤ እኛ ደግሞ ከእናንተ ጋር እንድንነግሥ ብትነግሡ መልካም ይሆን ነበር።*
*ለዓለም ለመላእክትም ለሰዎችም መጫወቻ ሆነናልና፤ እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያቱን ሞት እንደ ተፈረደባቸው ሰዎች ከሁሉ ይልቅ የኋለኞች እንዳደረገን ይመስለኛልና።*
*እኛ ስለ ክርስቶስ ሞኞች ነን እናንተ ግን በክርስቶስ ልባሞች ናችሁ፤ እኛ ደካሞች ነን እናንተ ግን ኃይለኞች ናችሁ፤ እናንተ የከበራችሁ ናችሁ እኛ ግን የተዋረድን ነን።*
*(1ኛ ቆሮንቶስ 4፡7-10)*

በዚህ ምንባብ ጳውሎስ ይህንን የቆሮንቶስን ሰዎች ግትር አስተሳሰብ አላግጦበታል፡፡ እነርሱ የሚያስቡት በጥበባቸው ሥልጣንና ክብርን እንደተቀበሉ ሲሆን፣ በእርግጥ እነዚያን የሰጣቸው ግን ክርስቶስ ነበር፡፡ የክርስቶስ እውነተኛ ተከታዮች አንድ ቀን ከእርሱ ጋር በታደሰችው ምድር እንደሚነግሱ ያውቃሉ፣ እነርሱ ግን ክርስቶስ ንጉሥ ሆኖ ባይመጣም፣ አሁን ንግሥናቸውን መለማመድ እንደጀመሩ አድርገው የሞኝነት ሃሳብ ያስቡ ነበር፡፡ ስለዚህ ለክርስቶስ ብቻ የተገባውን ጥበብ፣ ብርታትና ክብር የራሳቸው አድርገው ይቆጥሩ ነበር፡፡

በአንዳንድ ነገሮች ረገድ፣ እነዚህ ግድፈቶች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ይታወቃል፡፡ ክርስቶስ ምድርን እንደገና ሲያድስ በአዲሲቷ ምድር አማኞች እንደሚነግሡ የቆሮንቶስ ሰዎች በትክክል ተረድተዋል፡፡ አማኞችም አሁን በሚመሩት ሕይወታቸው መሰረት ዘላለማዊ ብድራትን እንደሚቀበሉ በትክክል ተረድተዋል፡፡ የመንግሥቱም የመጨረሻ እርከን አስከተገለጠ ድረስ፣ እንደከበሩና ብድራታቸውንም እንደተቀበሉ ቢያስቡ ግር አይልም፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ ክርስቶስ በሚጠበቀው የታደሰ መንግሥት ውስጥ የትም ስፍረ በዐይን አስካልታየ ድረስ፣ የእርሱን የገዢነት ስፍራ በመተካት ገዢ መሆን እንዳለባቸው ማሰብ ለእነርሱ ቀላል ነው፡፡

ሆኖም ግን ስህተቱ ሊፈጠር እንደሚችል ቢታወቅም፣ ተቀባይነት ግን ፈጽሞ የለውም፡፡ እንዲያውም፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ በሥልጣን ላይ ያልሆኑትን አማኞች በማቃለላቸውና በመጉዳታቸው ትልቅ ጥፋት እየፈጠሩ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ይህንን ችግር ለማረም፣ መጪው ዘመን ገና በሙላቱ አልተገለጠም የሚለውን እውነታ ጳውሎስ አፅንዖት ሰጥቶበታል፡፡ ስለዚህ፣ ማንም ሰው "መንገሥ አልጀመረም"፡፡ ሁሉም ሰው የክርስቶስን መመለስ እየተጠባበቀ ነው፡፡

የቆሮንቶስም ሰዎች ክርስቶስ እንደ አዳኝ ያለውን ድርሻ በማቃለል ተገቢውን ክብር አልሰጡትም፡፡ በተለይም፣ አማኞች የመጪውን ዘመን በረከቶች ማለትም መንፈሳዊ ስጦታዎችንም ሆነ ክብርን ሊቀበሉ የሚችሉት ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆን ብቻ እንደሆነም ጠፍቶባቸዋል፡፡ ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆን፣ አማኞች የክርስቶስ ማንነትና ክብር ተካፋዮች ይሆናሉ፡፡ በዚህም ምክንያት፣ እግዚአብሔር የሚያያቸው በክርስቶስ ውስጥ ነው፣ ስለዚህ በቤተክርስቲያን ውስጥ እርሱን ሥልጣን፣ ክብርና ስጦታዎች እንዲቀበሉ አስችሏቸዋል፡፡

ሆኖም በአብዛኞቹ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ልቦና ውስጥ፣ ስጦታዎችና ክብር በእያንዳንዱ አማኝ ጥረት እንደሚገኝ ይታሰባል፡፡ ክርስቲያኖች ተፅዕኖ በመፍጠር ሥልጣን ከያዙ፣ ያ የሆነው ያ ሰው ስለሚገባው ነው ብለው ያስባሉ፡፡ አንድ አማኝ ያንን የመሰለውን ታዋቂነት ማግኘት ካቃተው ግን፣ እርሱ ወይም እርሷ አናሳ ክርስቲያኖች በመሆናቸው ምክንያት ነው ይላሉ፡፡

ስለዚህም ጳውሎስ፣ ለዚህ ስህተታቸው ምላሽ የሰጠው ሌላኛውን የነገረ-ፍፃሜውን ገፅታ በማንሳት ሲሆን አፅንዖት የሰጠውም በክርስቶስ ወሳኝነት ላይ ሲሆን፣ በተለይም በክርስቶስና በአማኞች መካከል ባለው አንድነት ላይ አተኩሯል፡፡ በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡15-17 ጳውሎስ ነጥቡን ግልጽ ያደረገበትን መንገድ እናድምጥ፡

*በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው*

*እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ።*
*ስለዚህ እኛ ከአሁን ጀምሮ ማንንም በሥጋ እንደሚሆን አናውቅም፤ ክርስቶስንም በሥጋ እንደ ሆነ ያወቅነው ብንሆን እንኳ፥ አሁን ግን ከእንግዲህ ወዲህ እንደዚህ አናውቀውም።*
*ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል። (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡15-17)*

አማኞች ራሳቸውንም ሆነ ሌሎችን በዓለማዊ ወይም በሥጋዊ መመዘኛዎች መመዘን እንደማይገባቸው ጳውሎስ ያሳስባል፡፡ ይልቁኑ፣ አማኞችን ሁሉ ከክርስቶስ ጋር አንድ እንደ ሆኑ ህዝቦች እንዲመለከቱና ጌታን እንደሚያከብሩ ሁሉ አንዳቸው ሌላቸውን እንዲያከብሩ ይፈልጋል፡፡ እንዲያውም፣ ጳውሎስ ይህንን ምክንያቱን ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ ደግሞ ደጋግሞ እያሰመረበት ገልፆታል፡፡ በዚህ ረገድ በ1ኛ ቆሮንቶስ 8፡11-12 የሰጠውን ምክር እናድምጥ፡

*በአንተ እውቀትም ይህ ደካማ ይጠፋል፥ እርሱም ክርስቶስ የሞተለት ወንድም ነው።*
*እንዲህም ወንድሞችን እየበደላችሁ ደካማም የሆነውን ሕሊናቸውን እያቆሰላችሁ ክርስቶስን ትበድላላችሁ። (1ኛ ቆሮንቶስ 8፡11-12)*

አማኞች ከክርስቶስ ጋር አንደ ከመሆናቸው የተነሳ፣ በአንድ አማኝ ላይ በደል መፈፀም በክርስቶስ ላይ ኃጢአት እንደመሥራት እንደሚቆጠር ጳውሎስ ያስተምራል፡፡ እናም በጌታ ራት ወቅት ባለጠጎቹ ድሆቹን እንዳያሳፍሯቸው መመሪያ ሲሰጥ ተመሳሳይ የሆነውን መሞገቻውን ያነሳል፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ 11፡24-27 እንዲህ ጽፏል፡

*ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፥ ቆርሶም፦ እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።*
*እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ፦ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።*
*ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።*
*ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት። (1ኛ ቆሮንቶስ 11፡24-27)*

ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን የሰጠው ለሁሉ እንጂ ለኃያላኑና ለባለጠጎቹ ብቻ እንዳልሆነ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች ያሳስባቸዋል፡፡ ስለዚህ አማኞች በጠቅላላ የመጪውን ዘመን በረከቶች የሚቀበሉት በክርስቶስ አማካይነት ብቻ ነው ይህም ሁሉም እኩል ተካፋዮች ናቸው ብሎም ያሳስባቸዋል፡፡ በመጨረሻም፣ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ራስን የበላይ በማድረግ በጌታ ራት ወቅት ድሆችንና ሌሎች አማኞችን ማቃለል፣ በኢየሱስ ላይ ኃጢአት መሥራት ነው ይላቸዋል፡፡

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ፣ ሌሎችን አማኞችን የማክበር፣ ዋጋ የመስጠትና የማገልገል መሠረቱ ከክርስቶስ ጋር ያለን አንድነት መሆኑን ደጋግሞ አመልክቷል፡፡ ይህንንም በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡12 ውስጥ የሰውነታችን ብልቶች አንዳቸው በሌላቸው ላይ የተደገፉ እንደሆኑ ሁሉ አማኞችም እርስ በርስ መደጋገፍ እንዳለባቸው አሳይቷል፡፡ ደግሞም አማኞች የክርስቶስን መጽናናት እንደሚካፈሉ በገለጠበት በ2ኛ ቆሮንቶስ 1፡5 ውስጥ ደግሞ አንስቶታል፡፡ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ውስጥ ስለ እነዚህ ሃሳቦች

የጠቃቀሳቸውን ሁሉ ለመዘርዘር ሰዓት ስለማይበቃን አስተሳሰቡን እንዲህ ብለን በማጠቃለል ራሳችንን መገደብ መርጠናል፡ አማኞች የመጪው ዘመን በረከቶች ተካፋይ የሚሆኑት ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆን ብቻ ነው፡፡ እኛም ይህንን ስንገነዘብ፣ ለክርስቶስ የሚገባውን ክብር እንሰጣለን ደግሞም ከልብ ክፋት ከሚመነጨውም ኃጢአት እንርቃለን፡፡

## ተስፋ

ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎችን ነገረ-ፍፃሜ ለማረም የሞከረበት ሁለተኛ መንገድ የበረከታቸውን ጊዜያዊ ተፈጥሮ እንዲያስታውሱ ማድረግ ነው፡፡ ምንም እንኳን የቆሮንቶስ ሰዎች የሚመጣውን ዘመን በረከቶች ማጣጣም ቢጀምሩም፣ ኃጢአትና ሞት ያለበት የአሁን ዘመን ገና አልተወገደም፡፡ ለምሳሌ፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ 7፡31፣ ጳውሎስ እንዲህ ጽፏል፡

> ***… የዚች ዓለም መልክ አላፊ ነውና። (1ኛ ቆሮንቶስ 7፡31)***

በ1ኛ ቆሮንቶስ 2፡6 ውስጥም ተመሳሳይ ሃሳብ አስፍሯል፡

> ***… የሚሻሩትንም የዚችን ዓለም ገዦች ጥበብ አይደለም (1ኛ ቆሮንቶስ 2፡6)***

በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡50 ደግሞ፡

> ***ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፥ (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡50)***

እርግጥ ነው የቆሮንቶስ ሰዎች ሥጋና ደም መሆናቸውን ያውቃሉ፣ ስለዚህ በዚህ ማንነታቸው የተሟላውን ዘላለማዊ በረከታቸውን ሊቀበሉ እንደማይችሉ ይህ ሃሳብ ያመለክታቸዋል፡፡ በተመሳሳይም፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ 4፡8 ውስጥ የቆሮንቶስ ሰዎች ከክርስቶስ ጋር መንገሥ እንዳልጀመሩ ጳውሎስ ይሞግታቸዋል፡፡ ይህ ጉዳይ በመጪው ዘመን የምናጣጥመው ሕይወት አንዱ ገፅታ ነው፡፡

አስተምህሮተ ተስፋን አስመልክቶ ጳውሎስ በቀጥታ ተዛምዶ ከሰራባቸው ረጃጅም ዐረፍተ-ነገሮቹ መካከል በጣም ረጅሙ የሚገኘው በ1ኛ ቆሮንቶስ 15 ውስጥ የሚገኘው ነው፡፡ በዚያም፣ ወደፊት የሚከናወነውን የአማኞች አካላዊ ትንሣኤ የሚክዱትን ተጋፍጧቸዋል፡፡ እንደተመለከትነው፣ ከቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን አማኞች መካከል ቢያንስ ጥቂቶቹ የመጪውን ዘመን በረከቶች አሁን ማጣጣም እንደጀመሩ ያምናሉ፡፡ በተጨማሪም የመንግሥቱ በረከቶች አሁን በሙላት እዚህ ስለተገኙ፣ ወደፊት የምንጠብቀው ምንም የለም ብለውም ያምናሉ፡፡ ሆኖም በ1ኛ ቆሮንቶስ 15 ውስጥ ግን፣ ጳውሎስ መጪው ዘመን በሙላት ከመገለጡ አስቀድሞ፣ በጣም ግዙፍ የሆኑ ክንውኖች ሊከናወኑ ግድ እንደሆነ፣ እጅግ አስደናቂና ወሳኝ የሆኑ ለውጦችም ሊከናወኑ እንደሚገባ በግልጽ ያስቀምጥላቸዋል፡፡ እነዚህንም ለውጦች በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡22-24 እንዲህ ጠቅለል አድርጎ አቅርቦታል፡

> ***ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና።***
> ***ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል፤ ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው፥ በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው፤***
> ***በኋላም፥ መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ ኃይልንም በሻረ ጊዜ፥ ፍጻሜ ይሆናል። (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡22-24)***

ክርስቶስ ከሞት እንደተነሣ ሁሉ፣ አማኞችም ከሞት ሊነሡ ይገባል፣ ትንሣኤ የሚያገኙት ግን ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመለስ ብቻ ነው፡፡ ከዚያም፣ በከበረው ሰውነታቸው ከእርሱ ጋር ለዘላለም ይኖራሉ፡፡ የእርሱ መመለስና የእነርሱ ትንሣኤ የአሁኑ ዘመን ከግዛቱ፣ ከሥልጣኑና ከኃይሉ ጋር ያከተመ መሆኑ ማረጋገጫ ነው፡፡

ክርስቶስ ዳግመኛ እስካልተመለሰ ድረስ፣ ትንሣኤም እስካልተከናወነ ድረስ፣ የቆሮንቶስ ሰዎች ምንም ያስቡ ምንም፣ ገና ሙሉ ክብራቸውን ሊያገኙ አይችሉም፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡19 እንዲህ ጽፏል፡

> ***በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ፥ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን። (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡19)***

ስለ አሁኑ ዓለም ጊዜያዊ መልክ በግልጽ ከተናገረ በኋላ፣ የቆሮንቶስ ሰዎች አሁን ስለሚኖሩበት ሕይወትና ስለ ቤተክርስቲያናቸው ትክክለኛና በእውነታ ላይ የተመሠረተ አመለካከት እንደሚኖራቸው ጳውሎስ ተስፋ ያደርጋል፡፡ ይህም አዲስ አስተሳሰብ ከዚህ ቀደም ስላሳለፉት የኃጢአትና የዕብሪት ሕይወት ንስሓ እንደሚገቡም ተስፋ ያደርጋል፡፡

## ፍቅር

ከጳውሎስ ነገረ-መለኮታዊ አመለካከቶች መካከል በመጨረሻ የምናነሳው የፍቅርን አስፈላጊነት ነው፡፡ በጥቅሉ፣ ፍቅር የእግዚአብሔር ህግጋት ፍፃሜ ወይም መጠቅለያ እንደሆነ እናምናለን ወይም ታላቁ ትዕዛዝ እንደሆነ እናስባለን እንጂ፣ የነገረ-ፍፃሜ ውቅረ-ነገር እንደሆነ አናስብም፡፡ ሆኖም፣ ፍቅር ለአሁኑ ዓለምም ሆነ ለመጪው ዓለም እጅግ ወሳኝ የመሆኑ ነገር እውነትነት እንዳለው ሁሉ፣ ፍቅር የነገረ-ፍፃሜም ክቡር አካል የመሆኑ ነገር ለጳውሎስ ብርቱ እውነት ነው፡፡ ያም ማለት፣ ፍቅር የጳውሎስ የመጨረሻው ዘመን ነገረ-መለኮት ቁልፍ አካል ነው ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ፣ በታወቀውና በተለምዶ የፍቅር ምዕራፍ ብለን በምንጠራው በ1ኛ ቆሮንቶስ 13 ውስጥ፣ ጳውሎስ ስለ ፍቅር የከበረ ዋጋ ያቀረበውን ሙግት እንመልከት፡፡ ከቁጥር 8-10 ድረስ እንዲህ ሲል ጽፏል፡፡

> ***ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል።***
> ***ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና፥ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና፤***
> ***ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል። ... እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።***
> ***(1ኛ ቆሮንቶስ 13፡8-10፣13)***

ነጥቡም መጪው ዘመን በሙላት ሲመጣ በአሁኑ ዘመን የምናያቸው የሕይወት ገጽታዎች አብዛኞቹ ይወገዳሉ የሚል ነው፡፡ ትንቢትም ሆነ የእውቀት ስጦታ ምንም ጥቅም አይኖራቸውም ምክንያቱም እነርሱ ያመለከቷቸው ነገሮች በዐይናችን ፊት ተገልጠው ስለሚታዩ ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይም፣ በክርስትና ሕይወት ውስጥ የከበረ ስፍራ ያላቸው እምነትና ተስፋም መጪው ዘመን በሙላት ሲገለጥ ስፍራ የላቸውም ማለት ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጳውሎስ ከጠቀሳቸው የክርስትና ሕይወት ድንቅ ገፅታዎችና መንፈሳዊ ስጦታዎች ሁሉ በመጪው ዘመን ሙላት ውስጥ የሚገለጠውና አብሮን የሚኖረው ፍቅር ብቻ ነው፡፡ አሁንም ያን ጊዜም እንወድዳለን፡፡ አሁን ተወድደናል ያንጊዜም እንወደዳለን፡፡ ፍቅር በራሱ በመጪው ዘመን በረከቶች ውስጥ ተሳታፊ መሆን ነው፡፡ እንዲያውም፣ ፍቅር የእነዚያ በረከቶች ዋና መገለጫ ነው፡፡

ጥያቄው ግን ጳውሎስ ይህንን የፍቅር ነገረ-መለኮታዊ ፋይዳ ከቆሮንቶስ ችግሮች ጋር ያዛመደው እንዴት ነው? የሚለው ነው፡፡ ይህንን ያደረገባቸውን በርካታ መንገዶች አስቀድመን ዐይተናል፡፡ ለምሳሌ፣ ደካማ ክርስቲያኖች እነርሱን በማየት በጣዖት አምለኮ ውስጥ ለመካፈል እንዳይበረታቱ ለማድረግ በእምነት ጠንካራ የሆኑቱ በጣዖታት መቅደሶች ውስጥ ሥጋ ከመብላት እንዲታቀቡ አበረታትቷል፡፡ ይህንን ጉዳይ በ1ኛ ቆሮንቶስ 8፡1 እንዲህ ሲል ጠቅሶታል፡

*ለጣዖት ስለ ተሠዋ ሥጋም፥ ሁላችን እውቀት እንዳለን እናውቃለን። እውቀት ያስታብያል ፍቅር ግን ያንጻል። (1ኛ ቆሮንቶስ 8፡1)*

በሌላ አገላለጽ፣ ለጣዖት የተሰዋን ሥጋ ስላለመብላት ያነሳው መከራከሪያ እንዴት ማፍቀር እንዳለብን የሚያሳይ ነው፡፡

ጳውሎስ ስለ ሐዋርያዊ ሥልጣኑ ሙግቱን ሲያቀርብም ስለ ፍቅር በብርቱ ተናግሯል፡፡ ለምሳሌ፣ ለምን አሁን እያገለገለ ባለበት መንገድ እንደሚያገለግል ሲያብራራ፣ በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡14-15 እንዲህ ጽፏል፡

***ይህን ስለቆረጥን የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና፤ አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ፤ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ፤***
***በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ። (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡14-15)***

ጳውሎስ ስለ ፍቅር ያነሳቸውን ሃሳቦች በቀጥታ ከቆሮንቶስ ችግሮች ጋር አያይዞ የገለጠበት መንገድ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች የሰጠው መመሪያ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ስጦታውን በአስደናቂ መንገድ ቢያፈስስላቸውም እንኳን፣ አስደናቂ ስጦታዎች ማለትም በልሳን የመናገርና የትንቢት ስጦታ አለን የሚሉት ሰዎች፣ ትንግርታዊ ስጦታ ያልተቀበሉት ሰዎች አናሳ እንደሆኑ ወደማሰብ ትዕቢት ውስጥ ገብተው ነበር፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ ይህንን ጉዳይ ለማከም ከተጠቀመባቸው መንገዶች አንዱ፣ አስደናቂዎቹም ሆኑ ሌሎቹ ስጦታዎች በፍቅር አገልግሎት ላይ አስካልዋሉ ድረስ ምንም ጥቅም እንደሌላቸውና ይልቁኑም የሚያበሳጩ እንደሆኑ መግለጥ ነበር፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ 13፡1-2 እንዲህ ሲል ጽፏል፡

***በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሽዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ።***
***ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።***
***(1ኛ ቆሮንቶስ 13፡ 1-2 )***

ትንቢት፣ በልሳን መናገር፣ መለኮታዊ እውቀት እና ተዓምር-የማድረግ እምነት በዓለማዊ እይታ ሲመዘኑ አስደማሚ ናቸው፡፡ እውነቱ ግን፣ የተሰጡት ለአማኞች መንፈሳዊ እድገት ነው እንጂ፣ ለዓለማዊ ጥቅሞቻቸውና ለራሳቸው ደስታ አይደለም፡፡ መንፈሳዊ ስጦታዎች በፍቅር ካልተገለጡ፣ መንፈሳዊ በረከቶችን ሊያመጡ አይችሉም፡፡ እነዚህ ስጦታዎች የአሁኑን ዓለም ስቃይና ሞት ሊያቀልሉ የሚችሉትና ቤተክርስቲያን በመጪው ዘመን በረከቶች ተካፋይ መሆን እንድትጀምር የሚያደርጓት በፍቅር ተግባር ላይ ሲውሉ ብቻ ነው፡፡

# 5. ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተነስተው ለነበሩ ችግሮች ጳውሎስ እንዴት ምላሽ እንደሰጠ ተመልክተናል፡፡ ከቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ጋር የነበረውን ግንኙነት ዳራ ደግሞም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲካተቱ የተደረጉትን ለእነርሱ የጻፋቸውን መልእክቶች ይዘትም ዳስሰናል፡፡ በመጨረሻም፣ ጳውሎስ ነገረ-መለኮቱን ከችግሮቻቸው ጋር እንዴት እንዳዛመደ አይተናል፡፡ ይህንንም ያደረገው፣ አማኞች ያለ ልክ የኃለውን ነገረ-ፍፃሜያቸውን መለስ ብለው እንዲቃኙ፣ ስለ በደላቸው ንስሓ እንዲገቡ፣ ትህትናን እንዲማሩ፣ እርስ በርስ እንዲከባበሩ እና ወደ ፊት የምትገለጠውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ሙላት በተስፋና በናፍቆት እንዲጠባበቁ ጥሪ በማቅረብ ነው፡፡

ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያንን ችግሮች መፍትሄ የሰጠበትንና በአጠቃላይ ቤተክርስቲያኒቱን ያስተናገደበትን መንገድ ስንመለከት፣ ነገረ-መለኮቱ ለችግሮቻቸው መፍትሄ የሰጠበት ወሳኝ መሣሪያ እንደሆነ እንገነዘባለን ለእኛም ትምህርት ይሆነናል፡፡ በርካታ ክርስቲያኖች ዛሬም ቢሆን ስለራሳቸው ማሰብ ከሚገባቸው በላይ የላቀ ግምት ይሰጣሉ፣ ስለ ስጦታቸውም ያለ ልክ ይመካሉ፣ ሕይወታቸውንም የሚቃኙት በግል ፍላጎቶቻቸውና መሻቶቻቸው አንፃር ነው፡፡ ዛሬ አብያተክርስቲያናት በማያቋርጥ ሁኔታ በመከፋፈልና አንጃ በመፍጠር ችግሮች ደግሞም በዝሙት ኃጢአቶች ይታመሳሉ፡፡ አንዳንዶቹም ጳውሎስን የመሳሰሉ የእግዚአብሔር ነቢያትና ሐዋርያትን መገለጦች ውድቅ ለማድረግና ለማናናቅ ይጥራሉ፡፡ ክርስቶስ ጳውሎስን አምባሳደሩ አድርጎ የጠራው እንድንንቀው አይደለም፣ ደግሞም የእኛ ነገር ከወደቀው ምድራዊ ዓለም ጥቅማችን ጋር ብቻ የተያያዘ እንዲሆንና በዚያ ብቻ እንድንረካ ለማድረግ ክርስቶስ በምድር ባልኖረና ስለ እኛ ባልሞተም ነበር፡፡ የጳውሎስን ነገረ-መለኮት ማዕከላዊ ልብ በትክክል ስናደምጥ፣ በክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ ሙላቱ የሚገለጠውን መጪ ዘመን ስንጠባበቅ፣ እርስ በርስ እንድንዋደድ እና በክርስቶስ ላይ እንድናተኩር የቆሮንቶስን ሰዎች እንዳሳሰበ ሁሉ እኛንም ያሳስበናል፡፡